## ለ. የአዲስ ምልስ ወያኔወች የማስመሰያ ኢትዮጵያዊ ተቆርቋሪነት፣

ከብ/ጄኔራል ኃይሌ መለሰ.

(ክፍል ሁለት፣ ካለፈው የቀጠለ)

በውል እንደሚታወቀው በዘረኝነት ተጸንሰው የተወለዱትና በዘረኝነት በተደገፈ እንክብካቤ አድገው ከዚህ ደረጃ ላይ የደረሱት የትግራይ ወያኔወች አቅደው የተነሱበት በዘረኝነት በሽታ የተበከለ መሠረታዊ ዓላማ ሁለት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የተነጣጠሩ ተልዕኮዎችን በማሟላት ላይ መሠረት ያደረገ ነው፣-

1. ታሪካዊ ጠላቶቻችን ለረጅም ዘመናት ሲድሁ የኖሩበትን እቅድ መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያ የምትባል አገርና ኢትዮጵዮጵያዊ የሚባል ሕዝብ በአንድነት እንዳይኖሩ ማድረግ ነው። የዋነኛው ግብ ማጠናከሪያ የሆነው ሌላው የዘመቻው አካል ወያኔወች የመጀመሪያወቹ ብቻም ሳይሆኑ የመጨረሻወቹም ለመሆን ዘምተው አንዲት አገር በራሷ ልጆች ተክዳ ስትጠፋ ምን እንደምትመስል ኢትዮጵያን ለቤተ-ሙከራ አቅርበው ለዓለም ሕዝብ ለማሳየትና ለዘመናት ተደርጎም ሆነ ተሰምቶ የማይታወቅ አዲስ የጉደኞች ጉድ ሊባልለት የተገባ ታሪክ ለማስመዝገብ ነው፤

2. ይህን እቅድ በማሳካት የታላቋን ታሪካዊት አገር ስምና ክብር የምትወርስና በእሷ ሐብትና ንብረት የምትገነባ ትንሿን ትግራይን ወደ ታላቅ ሪፐብሊክ አገር ለማሳደግ መሆኑን አቅደው በተነሱበት ዓላማቸውና ሲፈጽሟቸው በኖሩት የጠላትነት ድርጊቶቻቸው አረጋግጠውልናል። እምነት አልባ የሆነ የማስመሰያ ቃላቸውን እንደ እስስት ገላ እየለዋወጡ መጠቀም የማይገዳቸው የቀለም ኢትዮጵያዊያን አቅደው የተነሱበትን ዓላማ ለማሳካት ደደቢት ጫካ ውስጥ ገብተው የትጥቅ ትግል ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ በግልጽ ሲነገሩን የኖሩት እንዳልነበር ሁሉ ዛሬ ደግሞ በአዲስ ምልስ የማስመሰያ ኢትዮጵያዊነታቸው አዲስ ሰወች መስለው ያነኑ እምነትና አቋማቸውን በሌላ አባባል እየደረቱልን ነው። የተመልሰናል ባይነታቸው ሐቅ ግን በእምነት ሳይሆን ትላንት በጫካ ለበስ ሰውነታቸው ሲናገሩ የኖሩትን ቃል ለስልታዊ ጠቀሜታው ሲሉ ወደሚያመሳስላቸው የከተማ ሰውነት ተርጉመው መናገራቸው ብቻ ነው። ይህም ማለት መናገር የፈለጉትን ከሬት የመረረ ቃል ተናግረው ከጨረሱና ማድረግ የፈለጉትን ሁሉ አድርገው በሚፈልጉት ደረጃ ላይ ካደረሱ በኋላ ከእንግዲህ ወዲያ የሚገደንም ሆነ የሚገድበን የለም የማለት ዓይነት ነው።

በእርግጥ ኢትዮጵያዊ ሰውነት ተላብሰውና ወደ ኢትዮጵያዊነታቸው እንዲመለሱ የሚያደርግ ልቦና ሰጥቷቸው የተመለሱ ቢሆን ኖሮ እኛም እሰየ እንኳን ከምታመልኩት የክህደት ጣዖትና ያለምክንያት ካዘመታችሁ ጠላትነት ተላቃችሁ መጣችሁ ብለን በደስታ በተቀበልናቸው ነበር። ነገር ግን እንደ አለፉት ዓመታት ከበከላቸው በሽታ ጋር ተቀብለን ስናስታምማቸውም ሆነ የችግር ዳፋቸውን ሁሉ ተሸክመን ስንጎብጥላቸው ለመኖር ግን ለእነሱም የነተበ ቋንቋና ጊዜው ያለፈበት ስልት፣ ለእኛም ኢትዮጵያዊያን ኃይሎች ችለን የኖርንበት ሰፌ ትዕግስትና በስመ-የአገር ሰውነት ስንታለል የኖርንበት ድክመት ያበቃለት ይመስለኛል። "ከአገር ሆድ ይሰፋል" እንደሚባለው ሆኖ አብረን ለመኖር ስንል በሁለመናቸው እንቻላቸው ብንል እንኳ የትኛው የሚያስተማምን



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

እምነታቸው አስተማምኖ ሊያኗኑረን? የትኛው የሚፈቀር ፍቅራቸው አፋቅሮ ሊያስተቃቅፈን? የየትኛው መልካም ሥራቸው ውለታ ከብዶ ሊገዛንና ሲያደርጉብን የኖሩትን ክፉ ነገር ሁሉ ደምስሶ ሊያስረሳን? የትኛውስ ግብራቸው አቀራርቦ ሊያወያየንና የጋራ ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት አስተባብሮ ሊያዘምተን? ወዘተ የሚያሰኙ ብዙ ውስብስብ ጥያቄዎች በውስጡ ያሉበት ስለሆነ የሁል ጊዜ ተቺጋሪ ከመሆን የሚያላቅቅ መሠረታዊ መፍትሄን የሚፈልግ እንጅ እንዲህ በቀላሉ የሚታለፍ አይሆንም።

ለእኔ "ኢትዮጵያ የምትባል አገር አልነበረችም፣ አብረናችሁም አልኖርንም፣ ወርቅና አፈርም ከአንድ ላይ አይቀላቀልም..." ከመባል የከፋና የከበደ ከባዕድነትም አልፎ በዓላማና ድርጊት የተደገፈ የመረረ ጠላትነት ማራጋገጫ የሚሆነኝ ሌላ ቃል ፈጽሞ አላገኝለትም። በመጽሐፍ ቅዱስ "ሰው በአፉ የሚናገረው በልቡ ሞልቶ የተረፈውን ነው" እንደሚለው አቶ ስብሐት ነጋ (የወያኔወች አቦይ) ይህን ቃል የተናገሩት አዘውትረው ይዋዥበታል የሚባለው ውሀ ዘሏቸው ሳይሆን በሠፈራቸው ተጠንስሶ በሁሉም የእምነቱ ተከታዮች ሲብላላ የኖረውንና እድገቱን አሟልቶ የገነፈለውን የግባቸውን አመላካች ሂደት ይፋ አውጥተው ማረጋገጣቸው መሆኑ ሊያጠራጥረን አይገባም። እንግዲህ በአንድ በኩል ይህን ከሚሉን የወያኔ መሪወችና ሁለንተናዊ ድጋፍ እየሰጠ ከሚያጠናክራቸው የትግራይ ሕዝብ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በመዋደቅ ላይ ካሉት ኢትዮጵያዊያን አንዱ ከሆኑት ታላቁ ሰው አቶ ኦባንግ ሜቶና ዘግናኝ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ከተፈጸመበት የአኙዋክ ሕዝብ ማንኛቸው ኢትዮጵያን ተደላድለው እንደኖሩባትና አጣጥመጠው እንደተጠቀሙባት የሰው ዘር ዳኛ የሆነው አምላክ ፍርድ ይስጥበት ከማለት በአለፈ የክህደታቸውን አፈራራጅ ድርጊት የምገልጽበት ተመጣጣኝ ቃላት አላገኝለትም።

በአጠቃላይ ግን እነሱ አብረን የኖርንበትን የዘመናት ታሪክ የካዱ፣ የአገሪቱን ብሔራዊ አንድነት የናዱና እየተሳሰብን የኖርንበትን የፍቅር ማዕድ ገልብጠው የደፉ በመሆናቸው የሙጥኝ ብለን ብንለምናቸው እንኳ እነዚህ ሁሉ እየከሰሱ እንደ አውሬ ስለሚያስበረግጓቸው ከእኛ ጋር መኖርን አይፈልጉም። በተመልሰናል ሽፋን ሊሸነግሉን የሚፈልጉት ግን እስከ አሁን የፈጸሟቸው አረመኔያዊ ድርጊቶች ሳይወሱና ለትግራይ ሪፐብሊክ ግንባታ የጣሏቸው መሠረቶችም መለወጥ ቀርቶ ትንሽም እንኳ ሳይሸራረፉ ጠብቀንላቸው ዳር የሚዘልቁበትና የቀራቸውን አጠናቀው ለግባቸው የሚበቁበት ጊዜ ለመግዛት ሲሉ ብቻ ነው። እውን ከልባቸው ቢመለሱማ የመጀመሪያው እርምጃ በአገር ላይ ላደረሱት ጥፋትና በሕዝብ ላይ ለፈጸሙት እልቂት ሁሉ ጥፋትን አምኖ መቀበልና ምህርት መጠየቅ ነበር። እነሱ ግን አጥፊነታቸውን ማመን ቀርቶ መነቀፍን እንኳ አምርረው የጠሉ በመሆናቸው አሁንም በነበራቸው እምነትና አቋም የጸኑ የመሆናቸው እንጅ የመመለሳቸው ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም። ባለፉት 20 ዓመታት ለትግራይ ሁለንተናዊ ግንባታ ያዋሉት አልበቃ ያለ ይመስል የበለጠ ተጠቃሚ አድርጎ ለነጻነትና ለሉአላዊነት የሚያበቃ አረና ትግራይን መስርተው እየተደራጁ ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት ከሚታገሉ ኃይሎች ጋር አብረን እንታገላለን የሚሉን የድብብቆሽ ሚስጥርም ይኸው ነው።

ኢትዮጵያውያን ከኤርትራዊያን ጋር ወደፊት ግንኙነት ቢያደርጉስ የሚል ስጋታቸውን በሩቁ ለመከላከልና የመገናኛ ድልድዩ እንዳይጠገን ለማድረግ ሲሉ ፈቅደው ለአስረከቧቸው የአሰብ ወደብ ተቆርቋሪ መስለው ደጋግመው ከሚነግሩን ይልቅ በወረራ ስለያዟቸው የጎንደርና የውሎ የአስተዳደር ክልልና በግድ ትግሬ መሆን አልብህ ብለው ስለሚያሰቃዩት የአማራና የአገው ሕዝብ ያላቸውን የአቋም ለውጥ ነግረውን ቢሆን ኖሮ የእኛንም የዕምነት በር የሚከፍት ቁልፍ በሆነን ነበር። እነሱ አደራጅተው ያዘመቱት የአጋዚ ጦር በአገሪቱ ምዕራባዊ ክልል የሚኖረውን ሕዝብ እየጨፈጨፈ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

መሬቱን ለሱዳን አሳልፎ በመስጠት ላይ መሆኑን እያወቁ ጥፋቱ የማይመለከታቸውና አጥፊነቱ የማያስከስሳቸው ሆነው ከመታየት ይልቅ ማስቆም የሚቻልበትን እርምጃ ሊወስዱ በተገባቸውም ነበር። ወያኔወች በትግራይ ሕዝብ ተመክተው መኖር ብቻም ሳይሆን የእናት አገሩ ማጥፊያ መሳሪያ ሆኖ እያገለገላቸው መሆኑን ጠንቅቀው እያወቁ እሱ የለበትም እያሉ ከሚያስተባብሉ ይልቅ አንተም በውስጡ ያለህበት መሆንህን ስለምናውቅ ካሁን በኋላ ልታውቅበት ይገባል ብለው የዘለቄታውን መፍትሄ ሊነግሩት በተገባቸውም ነበር። የነጻ አውጭ ድርጅታቸውን ዓላማና የወንድሞቻቸውን ባህሪይ ጠንቅቀው እያወቁ ጅምራቸው እንዳይደናቀፍ ሕገ መንግሥታችን ለሰላማዊ ትግል አመች ሁኔታወችን ስለፈጠረ ሌላ አማራጭ የትግል ስልት ምን ሲል ታስቦ እያሉ ከሚከላከሉ ይልቅ እኛ ከተጠቀምንበት ስልትና ከተቆናጠጥንበት እርምጃ ውጭ ወያኔወች ሊወጡ የሚችሉበት መንገድና ሊወድቁ የሚችሉበት ስልት የለም ብለው ሐቁን ቢነግሩን ኖሮ እኛም ተመልስናል ባይነታቸውን በቅን ህሊና በአየንላቸውም ነበር። እንግዲህ እንዲህ ያለውን የፖለቲካ ቁማር እየተጫወቱ ለመቀጠል እራሳቸውን ካዘጋጁ ስልጡን አገር አፍራሾች ጋር አንድ ዓይነት የሚያስተማምን ብሔራዊ እምነትና የሚያግባባ የዓላማ ቁንቋ ኑሮን ሊያጠፉት አቅደው የዘመቱባትን አገር ሊያድኑልን ይችላሉ ብሎ ተስፋ ማድረግ የራስን ማንነት ፈጽሞ አጥቶ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው የጌታ ሥልጣን ወደ እነሱ ተላልፏል ብሎ እንደማምለክ የሚቆጠር የሞራል ዝቅጠት ውጤት ነው። እኔ ማን ነኝ? እነሱስ እነማንና ምን በማድረግ ላይ ያሉ ናቸው ብሎ እራሱን ለሚጠይቅ ኢትዮጵያዊ ግን (የስምና ቀለም ሳይሆን) እነሱን የሚያይበት ህሊና በአሁኑ ወቅት የሚናገሩትን የማስመሰያ ቃላት ሳይሆን ሲያመልኩ የኖሩትን ክህደትና ሲፈጽሙ የኖሩትን ድርጊት ከእነሱ በፊት አስቀድሞ እያነበበና ለዚያ ሁሉ የማይረሳ በደላቸው ምን ሊደረግ እንደሚገባ እያብሰለሰለ ነው።

በመሠረቱ በአንድ አገር ውስጥ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ቅራኔ መፈጠር፣ ወይም በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች መቸገር የነበረ፣ ያለና ወደፊትም ሊኖር የሚችል ነው። የእኛን አገር ችግር ከሌሎቹ ሁሉ የተለየ የሚያደርገው ማጥፋትን የመኖር ዋስትናቸው አድርገው የሚያመልኩ የዲያብሎስ እምነትና ግብር ተከታይ የሆኑ ጠላቶች ስለአጋጠሙን ነው። ጌታ ኢየሱስ አይሁዳውያንን ከኃጢአት ባርነት ነጻ ስለመሆን ሲያስተምር ***“እኛ የአብርሃም ዘር ነን፣ ከቶ ለማንም ባሪያ ሆነን አናውቅም፤ ታዲያ አንተ ነጻ ትወጣላችሁ የምትለን እንዴት ነው?”*** ብለው ***ይጠይቁታል። ጌታም “በእውነት እላችኋለሁ ኃጢአት የሚሠራ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው፤...የአብርሃም ልጆችስ ብትሆኑ ኖሮ የአብርሃምን ሥራ በሠራችሁ ነበር፣...እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ፤ ፍላጎታችሁም የአባታችሁን ምኞት መፈጸም ነው። እሱ ከመጀመሪያው አንስቶ ነፍሰ ገዳይ ነበር። እውነት በሱ ስለሌለ ከእውነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እሱ ሐሰተኛና የሐሰት አባት ነው...”*** ብሎ እንደመለሰላቸው በዮሐንስ 8፣31-44÷ተገልጿል። ከመንፈሳዊ መልዕክቱ አንጻር የወያኔዎች ዓላማና ድርጊት ሲገመገም ሁለመናቸውን እንደ መስታውት ገላልጦ የሚያሳይ ነው።እነሱ ከስጋ ቆጠራ ባለፈ በእርግጥም የእነዚያ ታላላቅ ሰዎች ዮሐንስና  አሉላ የባህሪይ ልጆች ባለመሆናቸው ከአባታቸው ከዲያብሎ በወረሱት እምነትና ግብር ምን በማድረግ ላይ እንዳሉ በችግራቸው እሳት ተጥዶ እየተጠበሰ የሚኖረው ሕዝብ ቀርቶ ገና በእናቱ ማህጸን የነበረው ህጻን እንኳ እየተሸማቀቀ ይኖርበት የነበርው ህይወቱ ስለሚነግረው የሚወለደው ደህና አድርጎ ካወቃቸው በኋላ ነው ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት በተፈጥሮ የታደለችው አገራችን ከዓለም የመጨረሻዎቹ ድሐ አገሮች ሞዴል፣በዓለም ላይ ያሉ ችግሮች ሁሉ መመራመሪያ ማዕከልና የሕዝቧ ማሰቃያና ማቃጠያ ሲያል፣ሕዝቧ ደግሞ ወልዶ እየሳመ የሚያሳድግ፣ እያስተማረ ለቁም ነገር የሚያበቃና በተማሩት



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ልጆቹ ሙያና እውቀት እየተጠቀመ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይዎቱን የሚለውጥ ሳይሆን ሲገደሉበት እያለቀሰ መቅበር፣ተነቅለው ሲሰደዱ እያዘነ መሸኘት፣በጫኑበት የችግር ቀንበር እየደቀቀ መኖር በተፈጥሮ የታደለውና ቋሚ ሥራው መስሎ እንዲታይ የተደረገው ችግርን ከችግር ጋር እያዳቀሉ ማራባት እንጅ ችገርን በመልካም ሥራ ተክቶ አገርንና ሕዝብን መጥቀም ታድሎ በሌላቸው በእርግጥም የዲያብሎስ ግብር ወራሽ በሆኑ የጥፋት መልዕክተኞች መዳፍ ስር በመውደቋ ነው።፣መንፈሳዊ መልዕክቱ በሰፊ ትርጉሙ ሲገናዘብ ግን የሁሉንም በር እያንኳኳ የየራሱን ህሊና እንዲመረምርና ተግባሩን እንዲለካ የሚያስገድድ ነው።ምክንያቱም ፊት ለፊት መጋፈጡ እንኳ ቢቀር ዓለም ለአወቃቸው ጠላቶቻችንና እነሱ በአገሪቱ ላይ ዘርተ ለአራቡት ብሔራዊ ችግር ቀጥ ያለ አቋም ያላችሁና የተሟላ ትርጉም የምትሰጡት ስንቶቻችሁ ናችሁ? የሚል ጥያቄ ቢቀርብ ስንቶቻችን ፈተናውን እንደምናልፍ አላውቅም።ስለሆነም በማንኛችንም ላይ ያተኮረው የወቅቱ ጥያቄ ኢትዮጵያ መወለድና ሌሎቹ እንደ ገበጣ ተጫዋቾቾ ቢከፋኝ ብመለስ እያሉ ሲገለባበጡ የሚኖሩባትን አገር ደጋግሞ መጥራት ሳይሆን ኢትዮጵያዊ እምነትን፣ ኢትዮጵያዊ ቃል ኪዳንንና ኢትዮጵያዊ የተግባር ሰውነትን አዋህዶ መግለጽ ሲችሉ ብቻ ነው።አለያማ ወላጆቹን በእምነትም ሆነ በባህሪይ የማይተካ ልጅ ነኝ ባይ ክዋናው አዝመራ እረግፎ እንደቀረ የገቦ እህል የሚቆጠር እንጅ የዋናው ምርት ዘር ነው ለማለት አያስችልም።ስለሆነም መምሰል የቅርጽ እንጅ የመሆን ይዘት ስለሌለው ኢትዮጵያዊነታቸውን የካዱ መጢቃወች ሁሉ የበልጉ ዝናብ አመችቷቸው ስለአበጡ ብቻ የአገር ሰውነት እምነት፣ስምና ክብር አላቸው ማለት አይደለም። ጎህ ቀዶ ሲነጋ፣የፀሐይዋ ሙቀት ሲጠርርና ነገሩ ሁሉ መልኩን ለውጦ ሲጠጥር ፈጥነው እንደሚጠወልጉ የማይቀር የተፈጥሮ ሕግ ነው።። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥት ነን እያሉ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ከዘመቱት የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ግንባር ቀደም መሪወች መካከል ሁሉንም መወከል የሚችሉትን አራቱን ብቻ በዋቢነት ጠቅሻለሁ።

በክፍል አንድ ከጠቀስኳቸው ጥቅሶች አንዱ ስለባሪያና የባሪያ ቤተሰቦች የሰውነት ክብር የለሽ ባሪያነት የሚገልጽ ነው። ልዑል እግዚአብሔር በአርዓያውና በአምሳሉ ሰውን ሲፈጥር ከአንድ አባትና እናት ተወልዶ እየተባዛ እንዲሄድ ያደረገው በእሱ ዘንድ አበላልጦ የፈጠረው ሰው አለመኖሩን ሊያረጋግጥልን ስለፈለገ ይመስለኛል። የሰው ልጅ ግን እንደተፈጥሮአዊ ታድሎው ሰላምን አጥብቃ በምትፈልገው ዓለማችን በሰላም አብሮ ከመኖር ይልቅ በራሱ ክህደት ክብሩን ተገፎ ለውድቀትና አሳር ከተዳረገው ሳጥናኤል ግብር በመወረስ በፈጠረው የልዩነት ጎራ ተሰላልፎ (አጥፊና ጠፊ በመኳኋን) ሲገዳደል መኖርን ወዶ ቀጥሎበታል። ይኸን ሁሉ በማዘከር ፈላስፋዎቹ ባሪያና ትውልደ-ባሪያ ያሏቸው በዚህ ሂደት ውስጥ በመንፈሳዊ ህይወታቸውና በማህበራዊ ኑሮዋቸው የቆሸሹትን፣ በስምና ታሪካቸው የጎደፉትንና ለመልካም ሥራ የሚያስመርጥ ተፈጥሮአዊ ታድሎ የሌላቸውን ትውልደ ባሪያወች ነው። ስለሆነም የፈላስፋዎቹን መልዕክት መሠረት በማድረግ የትግራይ ሕዝብና ወያኔወች እንደጣኦት የሚያመልኩትን መሪያቸውን የመለስ ዜናዊን ሲወራረስ የመጣ የዘረ ባንዳነት (ዘረ ባሪያነት) ታሪክ እንዳስበት።

መለስ ዜናዊ ባንዳ (ባሪያ) በሆኑ ወላጆቹ ተጸንሶ ባንዳ ሆኖ የተወለደ ነው። ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ እየሰማ የኖረውና ከተወለደም በኋላ መልካም ነገር የማይወጣውን አፉን የፈታው በባንዶች ቋንቋ ነው። እድገትና ትምህርቱም በባንዳ (በባሪያ) ርዕዮት እየተጠመቀ ነው። ስለዚህ የባንዳነት (የባሪያነት) እንጅ ሰው የሚያሰኝ የሰውነት ክብር የለውም። አባቱ ዜናዊ አስረስ ባንዳ ናቸው። አያቱ አስረስ ተሰማም ባንዳ ናቸው። ቅደመ አያቱም ተሰማ…ባንዳ ናቸው። የእናቱም ቤተሰቦች ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸው ናቸው። ከተዋለዱት ይልቅ የተጋቡት ይመሳሰላል እንደሚባለው የአዜብም የእንጀራ አባት ጎላ…(እንደ አቶ ገ/መድህን አርአያ ምሥክርነት ከሆነ ወላጅ አባቷ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ሱዳናዊ ነው) ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸው ናቸው ይባላል። ለዚህም ነው ሱዳን ሲሄድ የልጃችሁ ባል አማቻችሁ ነኝ፣ ሊቢያ ሲሄድ አረባዊ ነኝ፣ ጣሊያን አገር ሲሄድ የቤተሰቦቸን ሙያ የወረስኩ ዘረ ባንዳ ነኝ፣ ኤርትራ ሲሄድ ኤርትራዊ ነኝ፣ ትግራይ ሲሄድ ደግሞ ትግሬ ነኝ እያለ የሚኖር መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው። የፖለቲካ ትርፍ ያስገኝልኛል የሚል ግምት ካላደረበት በስተቀር (እንደባድሜ ጦርነትና ሁለተኛው ሽህ ዓመት አከባበር) ተሳስቶት እንኳ ኢትዮጵያዊ  ነኝ ብሎ ሲናገርና ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሲሰብክ  ሰምቻለሁ ብሎ ምስክርነት የሚሰጥለት አንድም ሰው አይገኝም። እንዲያውም እንኳን ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ በኩራት መናገርና ስለኢትዮጵያ ሊሰብክ ቀርቶ በደንብ ላስታዋለውና ለተከታተለው ሰው በየአጋጣሚው በሚያደርገው ዲስኩር ሁሉ ኢትዮጵያ የሚለውን ስም እጅግ አምርሮ ስለሚጠላ "**ኢትዮጵያ**" በማለት ፋንታ "**ሀገሪቱ**" ወይም "**ሀገራችን**" ሲል መኖሩን ማስተዋል ይችላል። ሌላው አንቀጽም ስለእኩይ ባህሪዩ ሲገልጽ “የአመጽ መጀመሪያው አመጽ ሠሪው አስቀድሞ ከበጎ ነገር ይርቃል፤ ሰውነቱን መጥፎ አመልን ያስለምዳታል። (ክህደትና ጫት) ከዚያ በኋላ የአመጽ ሥራው አንድ ባንድ እየተራባ (እየተጠራቀመ) ፍጻሜው መታማት ይሆንና ኃጢአቱ በጣም የበዛ ይሆናል። ስም አጠራሩም እየተደመሰሰ ይሄዳል” ይላል። ስለዚህ ከእንዲህ ያለው ዘረ-ባንዳ (ዘረ-ባሪያ) ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ምን የሚበጅ መልካም ነገር ይወጣዋል ተብሎ ሲጠበቅና እንደ ኢትዮጵያዊ ሰው ሲቆጠር እንደኖረ በብዙ የሚያጠያይቅ ነው። እሱ ግን ከዘሮቹ በወረሰው ሞያ ሳያፍርበትና በቅጥረኛ ባንዳነቱ ሳይሰጋበት ይኸውና የቀጣሪ ጌቶቹን ዓላማ ለማስፈጸም ሲል በቤተክርስቲያናችን፣ በእናት አገራችን፣ በሰንደቅ ዓላማችን፣ ለአገሪቱ አንድነት በጽናት በቆመው ሕዝብና በሚያገናኘው ቋንቋ፣ በአጠቃላይም አገሪቱን በሁለመናዋ ለማጥፋት በሚያስችለው እቅድ ላይ ተመሥርቶ የሚያደርገው መረባረብ የቅጥረኛ እቅድ አስፈጻሚነቱ ማረጋገጫወች ናቸው።

መልከ ጥፉወች መልከ መልካምችን ቀድመው ከማጥላላት የተሻለ ምርጫ የላቸውም እንደሚባለው ከእሱ የባሰ በአእምሮውም ሆነ በአካሉ ድሑርና ባሪያ ጠፍቶ ዓለም ያደነቃቸውንና ከ300 ሚ/ በላይ የሆነ ሕዝብ በሚኖርባት አሜሪካ የተመረጡትን ታላቅ ሰው "**የባሪያ መንግሥት ባይጎበኘን የሚቀርብን የለም**" ብሎ በአፈ-ቀላጤወቹ በኩል ማናገሩ መለስና አፈቀላጤዎቹ ምን ዓኢነት ሰዎች መሆናቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። አባባሉም ምንም እንኳን መለስ በዜግነቱም ሆነ በመሪነቱ ኢትዮጵያን ባይወክልም ከኢትዮጵያም አልፎ አህጉሩን አፍሪካን ጭምር የሚያሳፍር የማፈሪያወች ድርጊት መሆኑ ግልጽ ነው ። ሰሞኑን ደግሞ የባሪያነት ባህሪዩ እየነገሰበት ስለመጣ ትልልቅ ሰወችን ደደብ ብሎ ከመሳደብ ጀምሮ "ከአህያም ጋር መነጋገር እችላለሁ" እያለ ነው። ይህን ሲል ግን እውን ከአህያ ጋር መግባባት የሚችልበት ቋንቋ ኖሮት ሳይሆን አንድም ኮርቻ ጭኖ ከሚጋልባቸው ፕሬዚደንት ተብየወች፣ መፈናፈኛ በሌለው አዳራሽ ውስጥ እንደ በግ አጉሮ ለአገር ማጥፊያ ከሚገለገልባቸው የፓርላማ አባል ተብየ እቃወች በተቃዋሚነት ስም ከሚነግድባቸውና ካባቸውን ገልብጠው ከለበሱ አቋም የለሽ ቀበሌ አደንቋሪወች ጋር ከሆነ በእርግጥም እንደ አህያ ስለሚቆጥራቸውና እነሱም በዚህ መልክ እየታዩ ማገልገሉን ወደው ስለተቀበሉት በእሱ አባባል ልክ ሊሆን ይችላል። አባባሉ በሌላ መልኩ ሲተረጎም ግን አምርሮ የሚጠላውን ወገን ሰድቤ ላዋርደው ብሎ አስቦ እንደተናገረው ይገባናል። ነግር ግን ባለጌ እራሱን ሰድቦ ሲሰደብበት ይኖራል እንደሚባለው ከቅድመ አያቱ ጀምሮ ወርደትን ተሸክሞ የኖረ ዘረ-አህያነቱን በራሱ የህግ ምስክርነት ማረጋገጡ ግን የገባው አልመሰለኝም። በመሠረቱም የሰውን ልጅ አህያ (አድጊ) ማለት ሰው ቀርቶ አህያ እንኳ የማይሠራውን ድርጊት በመሥራት ላይ ያለን አህዮች እኛ ነን ብሎ የራስን አህያነት ከማረጋገጥ ባለፈ የሰው ልጅ የሆኑ ሰወች እንዲህ ስለተባሉ ብቻ የሰውነት ስምና ክብር ያጣሉ ማለት አይደለም። የዘለቄታ መፍትሄውም የእነሱን ወራዳ ባህሪይ ሲያስተናግዱ መኖር ሳይሆን



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ሰው የሆነ ሰው መሥራት የሚገባውን ሠርቶ ለሌላው የሰጡትን አድጊነት ለእነሱ መልሶ በመስጠት የእምነታቸው መግለጫና የግብራቸው ማረጋገጫ ስም ሆኖዋቸው እንዲኖር ማድረግ ነው። ለአገር መሪነት ቀርቶ እምነትን ለሚጠይቅ ለበር ዘበኛነት እንኳ የማይበቃው እውቅ ከሐዲ እስከ አሁን በጠላቶቿ ተገዝቶ ሲሸጣትና ሲለውጣት የኖረው ኢትዮጵያን ብቻ ነበር። በአሁኑ ወቅት ደግሞ አህጉሩን አፍሪካን በሙሉ ኮፐንሐገን (ዴንማርክ) ይካሄድ በነበረው የዓለም የአየር ንብረት ጉባኤ ላይ ያለመድህናን ድርድር ሸጧቸው በመመለሱ የዓለም ትኩስ ዜና ሆኖ ሰንብቷል። ለነገሩ እሰየ እንኳን ዳፋው ደረሰባችሁ የሚባልላቸው እንጅ የሚታዘንላቸው አይደሉም። ምክንያቱም በእምነት ባይወክላትም በስም እንኳ ጠ/ሚኒስትር እየተባለ ከሚጠራባት አገርም አልፎ የአባይ ተፋሰስ አገሮችን ጭምር ለግብጽ አሳልፎ እንደሸጣቸው እያወቁ ለአህጉሩ ለአፍሪካ ይሆናል ብለው ወክለው መላካቸው ነው።

በእጅጉ የሚያሳዝነው ግን ይኸን ሁሉ ጠንቅቆ የሚያውቀው የትግራይ ሕዝብ እንዲህ ያለውን ሁለንተናዊ ማፈሪያ ተሸክሞ መኖሩና የጥፋት ዓላማው ማስፈጸሚያ መሳሪያ ሆኖ ማገልገሉ ነው። የትግራይ ሕዝብ በተጠያቂነት ቀርቶ በተጠቃሚነት የለበትም ብለው የሚከላከሉለት ወገኖች እንኳ ቢሆኑ መለስ ዜናዊን ግን እንዲህ ያለ ዘረ ባንዳ መሆኑን አናውቅም ብለው የሚያስተባብሉለት አይመስለኝም። ስለዚህ ይህን ሁሉ እያወቀ አገር አጥፊ ባንዳ አቅፎ ደግፎ በመያዝ እያሞካሸ በኢትዮጵያ ላይ አንግሶ ሲፈጽም ለኖረው ማናቸውም ውድመት፣ ጥፋትና እልቂት ሁሉ እጥፍ ድርብ ተጠያቂ ያደርገዋል። በአሁኑ ወቅት ብዙ የማስመሰያ ቃላት እየነገሩን ያሉት የወያኔ ባለስልጣኖችም ቢሆኑ ታሪኩን ከመነሻው ጀምሮ ከእኛ በበለጠ ጠንቅቀው እያወቁ እርስ በርሳቸው ከሚያናክሳቸው የጥቅም ግጭት ባለፈ ትላንት ቀርቶ ዛሬ እንኳ ከእውነተኛው የሕግ ምስክርና ኢትዮጵያዊ ሰው አቶ ገ/መድህን አርዓያ በስተቀር እንዴት ከዚህ ፀረ-ኢትዮጵያዊ ከሆነ ዘረ ባንዳ ጎን ተሰልፈን በእናት አገራችንና በወገናችን ላይ እንዘምታለን ብለው የተጸጸቱበት ወቅትም ሆነ አጋጣሚ አልነበረም፤ ዛሬም የለም። እሱን ከእነጥፋት ዓላማው ለመታገል ቁርጠኛ ሆኖ መነሳት ቀርቶ የፈጸመውን  እኩይ ድርጊት ለመግለጽ እንኳ ምላሳቸው እንጅ ህሊናቸው ዝግጁ አይደለም። የአንዳንዶቹን ተመልሰናል ባዮች እምነትና አቋም አጠያያቂ ከሚያደርጉት መሠረታዊ ነጥቦች አንዱም ይኸው ነው። በዚህ ጥያቄ ስር ወድቀው ከሚታዩት የወያኔ ባለስልጣኖች መካከል ለማገናዘብ ያህል የሦስቱን ብቻ ጠቅሻለሁ።

1. የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት መሥራችና የመከላከያ ሚኒስትራቸው የነበሩት አቶ ስየ አብርሐ እንደ አለቃቸው በዘረ ባንዳነት ባይፈረጁም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ሲያካሂዱ በኖሩት ዘመቻ ግን እንዲያውም በበለጠ ውድመትና እልቂት ያደረሱ ግንባር ቀደም ወንጀኛ መሆናቸው በብዙ ደጋፊ መረጃወች የተረጋገጠ ነው። የእናት አገርን አካል ከማስገንጠልና የባህር በሯን ከማዘጋት ጀምሮ በአርባ ጉጉ፣ በበደኖ፣ በጎንደር…ወዘተ ከፈጸሙት ትውልድ የማይረሳው ዘግናኝ እልቂት ጋር ተዳምሮ ሲታይ ከበቂ በላይ የሆኑ የማንነታቸው ማረጋገጫወች ናቸው። እንዲህ ያሉ ሰብአዊነት ያልፈጠረባቸው አረመኔም በመሆናቸው **"እኛ ከፈለግን ጦርነት መፍጠር እንችላለን፤ እኛ መግዛት ካልቻልንም የተበጣጠሰች አገር እናስረክባችኋለን"** ወዘተ እያሉ የሰጡንን ማስጠንቀቂያ ዘንግተንላቸው ከሆነ በእጅጉ ተሳስተናል። ዛሬ ደግሞ የጥቅም ግጭታቸውን ሽፋን በማድረግ በአዘጋጁት ተለዋጭ መድረክ ላይ አንፈራጠው ቁመው የነባር ቤታቸው መደላድል እንዳይነቃ ለማድረግ በሚያስችል ስልት **"ሕገ - መንግሥታችን ለሰላማዊ ትግል አመች ሁኔታወችን የፈጠረ ስለሆነ ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ የትግል ስልት መታሰብ የለበትም። ለፖለቲካዊ ችግርም መፍትሄ ፖለቲካዊ ውይይት ነው… ወዘተ"** የሚሉ  ሰበካቸውን እየለገሱን ናቸው።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ይህን መንገር የነበረባቸው ግን ከራሳቸው ጀምሮ አገሪቱንና ሕዝቧን ማጥፋት አማራጭ የሌለው የትግል ስልት ነው ብለው ለዘመቱ አጋሮቻቸው እንጅ ለእኛ አልነበረም። አባባላቸው በሌላ መልኩ ሲተረጎም ደግሞ ትላንት ድልድይ እያፈረሱ፣ ልማት እያወደሙና ባንኮችን እየዘረፉ፣ በጠላትነት የፈረጁትን ሕዝብ በጅምላ እየጨረሱና ቤተክርስቲያኖችን እያረከሱ የመጡበት ጎዳና ሁሉ እነሱ እስከ አደረጉት ድረስ ቅዱስነት ነበር ማለት ነው። በማፍረስ የተካነ ለግንባታ ስለማይሆን የአንድነትን መሠረት አናግተው እራሳቸውን በማስገባት አደላድለው ለማስቀመጥ የቻሉት በዚህ ተክህኖዋቸው ተጠቅመው ሳይሆን አይቀርም የሚል ከፍተኛ ጥርጣሬ አለኝ። የእነሱ አንድነት ፓርቲ ውስጥ መግባት አንድነቱ ለተናጋው አንድነት ማጥበቂያ ይሆናሉ ብሎ ማሰብ በእራሱ ክፍተቱን የሚሞላለት ሳይሆን የበለጠ ከፍቶ ክፉ ነገሮችን እያስገባ መከፋፋቱ እየሰፋ እንዲሄድ የሚያደርግ ይሆናል የሚል ስጋቴን ቀደም ሲል የገለጽኩትም በዚህ ምክንያት ነው።

2. ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸውና የትግራይ ገዥ የነበሩት አቶ ገብሩ አስራት ደግሞ **“የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማቸነፍ የሚችል ሕዝብ ነው። እንደነፍጠኞች ተንኮል ቢሆንማ ኖሮ ከኤርትራውያን ወንድሞቻችን ጋር አቆራርጠውን ነበር”** ያሉትን ታሪክ መዝግቦ አፈራራጅ ጊዜ እየጠበቀለት ነው። አቶ ገብሩ አስራት እንደዚያ ያሉትን የጊዜ እርዝመት የማይረሳቸውና የሁኔታወች መለዋወጥ የማይሽራቸው የትምክህት ቃላት የተናገሩት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያላቸውን ዝቅተኛ ግምትና የለየለት የጠላትነት መንፈስ ለመግለጽ አስበው መሆኑ ግልጽ ይመስለኛል። ዛሬም ቢሆን የበለጠ በሚያስባስባቸውና በሚያደራጃቸው መድረክ ላይ ሆነው ወያኔወች እስከ አሁን ለትግራይ ሕዝብ የሚፈልገውን ሁሉ ስለአላደረገለት የበለጠ ተጠቃሚ የሚያደርገውና በአንቀጽ 39 ታጅቦ ለነጻነትና ለሉአላዊነት የሚያበቃው አረና ትግራይ የተባለ አዲስ የመንደር ድርጅት እነዚያው መንደርተኞች በዚያችው መንደራቸው ለዚያችው መንደራቸው መስርተው በአዲስ ስልታዊ ዝግጅት መጣንባችሁ እያሉን ነው። ለእኔ እነዚህ ሁሉ **"ጧት ስትወጣ የመታህ እንቅፋት ስትመልስም ደግሞ ከመታህ ድንጋዩ አንተህ"** እንድሚባለው ካለፈው የማይማሩ ድንጋዮች ናቸው ተብለን የምንሰደብበት እንጅ የእነሱን ወገናዊነትና ከልባቸው መመለስ አያረጋግጥልኝም።

3. ሰሞኑን ደግሞ ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸውና እስከ ማሌሊት ምስርታ ጉባኤ ፍጻሜ የፓርቲያቸው መሪና የጦራቸው አዛዥ የነበሩት የትላንቱ አቶ የዛሬው ዶክተር አረጋዊ በርሄ የተባሉት በማስመሰያ ኢትዮጵያዊ ተቆርቋሪነት ከለላ ብቅ ብለው የእናንተ **“የኋልዮሽ ጉዞ አገራችንን ይበታትናል”** የሚል ማስጠንቀቂያ ለአንድነት ኃይሎች ሰጥተው እያስነበቡን ነው። ከመንደራቸው ውጭ በሩቁ እንዳያስቡና ተገላምጠው እንዳያዩ የሚያደርግ የዘረኝነት ወረርሽኝ የበከላቸው በሽተኞች ይህን ሲሉ 30 ዓመታት ሙሉ ስናካሂድ የኖርነው ባለብዙ ፈርጅ ማናጋትና እልቂት እንጅ የአንድነት ኃይሎች ችግሩን ለመከላከል የምታደርጉት ጥረት ከደደቢት ጫካ ጀምሮ አቅደን ከተነሳንበት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ዘመቻ ሊያድናቸው አይችልም ማለታቸው መሆኑ በጣም ግልጽ ነው። ማስጠንቀቂያ አዘል ለሆነው ጸረሑፋቸው ምክንያት ያደረጉት እኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመንፈስ ወክየ ለትግራይ ሕዝብ ያቀረብኩለትን የሁላችንም የሆነችውን እናት አገር ተባብረን የእናድን ጥያቄ በራሳቸው የጨለመ አመለካከት አይተው አዛበተው በመተርጎም ነው። በሽተኛወቹ ከእነሱ ሠፈር ውጭ የሆነውን ጤናማ እውነት ለይተው ማየት የሚችሉበት ዓይነ-ልቦና ባይኖራቸውም ለማስመሰል ሲሉ ያልተጠቀሙበት አባባልና ያላሉት ነገር የለም።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

መሠረታዊ ጥያቄው ግን ከእነዚያ ሁሉ ዝባዝንኬዎች ውስጥ እውነት መስለው መነበብ የሚችሉ ዐረፍተ-ነገሮች ቀርቶ እውነት መስላ መታየት የምትችለው ቃል የትኛዋ ናት? የሚለው ነው። በተለይም ለብሔራዊ አንድነታቸውና ለዳር ደንበራቸው፣ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው በመታገል ላይ ካሉት የአንድነት ኃይሎች ይልቅ የኢትዮጵያ መበታተን እኛን የበለጠ ያሰጋናል የሚሉን እነማን እንደሆኑ ለማወቅ አባባላቸውን በስፋት መዳሰስ አስፈላጊ ይሆናል። ይህን ስል ግን በአሸዋ ማሳ ላይ አረም ዘርተው የስንዴ ምርት እናፍሳለን ቢሉ እንኳ ህሊናቸውን ከማይከብዳቸውና ከማይገዳቸው የክህደት ሊቆች ጋር ታንቲራ ለመግጠም ፈልጌ ሳይሆን በእኔ ጥሪና በእነሱ ትርጉም መካከል ያለውን በሁለታችንም እምነትና አቋም ላይ የተመሠረቱ አባባሎቻችንን ለአንባብያን ጎን ለጎን አቅርቤ የህሊና ፍርድ እንዲሰጡበት ለማድረግ ነው።

## ለ.1. "<u>**የትግራይ ሕዝብ የሚያሳየው ሁኔታ ይሁንታ? ወይስ መስቀለኛ መንገድ ላይ የቆመ ዝምታ" በሚል ርእስ ባለፈው ያወጣሁት ጽሑፍ ዓላማ፣**</u>

በመሠረቱ በዚህ ርዕስ ሥር ያወጣሁት ጽሑፌ ዓላማ አራት አብይ መልዕክቶችን አጣምሮ የያዘ ነበር።

1. ከትግራይ ሕዝብ፣ ለትግርይ ሕዝብ፣ በትግራይ ሕዝብ ሁለንተናዊ ድጋፍ ከዚህ ደረጃ ላይ የደረሱት ወያኔወች ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን አጥፍተው የእሷን ስምና ክብር የምትወርስና በእሷ ሐብትና ንብረት የምትገነባ የትግራይ ሪፐብሊክን ለመነጠል በየፈርጁ በማካሄድ ላይ ያሉትን በተጨባጭ ማስረጃወች የተደገፈ ርብርቦሽ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማሳወቅ፤

2. መስቀልኛ መንገድ ላይ ቁሞ የእናት አገሩን ጥፋትና የወገኑን እልቂት በይሁንታም ይሁን በዝምታ ሲመለከት የኖረውን የትግራይ ሕዝብ ለምንና እንዴት እንዲህ ይደረጋል? ብሎ በግልጽ ለመጠየቅ በአጉል ይሉኝታ ተለጉሞ በመያዙ ምላሱ አልፈታለትና አንደበቱ አልተባለት ለአለው የአንድነት ኃይል ቁርጡን አሳውቄ አንድም ሊያረዱን በማዘጋጀት ላይ ያሉትን መርዶ አስቀድሜ ነግሬው ቁርጡን እንዲያውቅና እርሙን እንዲያወጣ፣ አለያም የእምነት አቋምህን መርምረህና የመሄጃ መንግድህን መርጠህ አሳውቀን የሚል ግልጽ ጥያቄ ለትግራይ ሕዝብ እንዲያቀርብና በተጓዳኝ መውሰድ የሚገባውን ቀጣይ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሁለንተናዊ ዝግጅት እንዲኖረው ለማሳሰብ፣

3. የችግሩን ዋነኛ ምንጭ ከነመነሻ ምክንያቱ በጥልቀት ከማወቅ ጀምሮ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ዘብ የቆሙ ኃይሎችንና የታሪካዊ ጠላቶቻችን እቅድ አስፈጻሚ ሆነው በሁለቱም ላይ የዘመቱትን ቅጥረኛ ባንዳወች ከእምነትና ግብራቸው ጎራ አኳያ አሰላልፎ በማፋለም በምሽግነት የሚገለገሉበትን የትግራይን ሕዝብ አራግፈውበት ሊሾልኩ ካከማቹበት ባለብዙ መልክ የችግር እዳ ነጻ ለማድረግ፣

4. በኢትዮጵያዊነቱ ሊወጣ ከሚገባው ግዴታ አኳያም በማሳሰቢያ መልክ ያቀረብኩለት ጥያቄወች፦

   4.1 በዚህ እጅግ ወሳኝ በሆነ ወቅት የእሱ ሚና በግልጽ መታወቅ የእሱም ጭምር በሆነችው እናት አገሩ ህልውና ብቻም ሳይሆን በወደፊቱ አብሮነትም ላይ የሚኖረው ገንቢ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

አስተዋጸኦ ልጆቹ ሊያቃቡት የፈለጉትን በቀላሉ ሊጠራ የማይችል የጥቁር ደም እዳ እንደ ጲላጦስ እኔን አልቀባኝም ብሎ እራሱን ነጻና ንጹህ አድርጎ ማሳየት የሚችልበት መልካም አጋጣሚ ነው ብየ አምናለሁ። (ገጽ 19)

4.2 ስለዚህ የትግራይ ሕዝብ የወያኔው መንግሥት አንድም ኢትዮጵያዊ ሆኖ የኢትዮጵያን ጥቅም ባያስጠብቅም የእኔ መንግሥት ነው ይል እንደሁ አቋሙን እንዲያሳውቅ፣ አለያም የእኔም አይደለም የሚል ከሆነ ደግሞ ከኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር ግንባር ፈጥሮ እንዲታገል ማሳወቅ ወቅቱ የማያልፈው አስገዳጅ ጥያቄ ሆኖ የቀረበለት መሆኑን ማወቅ አለበት።…የእኔ ጥያቄ የትግራይ ሕዝብ ይህን ሁሉ አስቦበት እንዲወስንና የልጅነት ግዴታውን ለእናት አገሩ እንዲወጣ የሚጠይቅ በመሆኑ በተቃራኒው ሊተረጎም አይገባም። (ገጽ 20)

4.3 እነዚህ ሁሉ ያለምንም ምክንያት በአንተ ልጆች የተፈጸሙ አፈራራጅ ክህደቶችና ወንጀሎች ናቸው። የተፈጸሙት ግን ባንተ ስምና መሳሪያነት ነው። ሊያራግፉብህ ካከማቹት ባለብዙ መልክ እዳ እራስህን ነጻ ማውጣት አለብህ ብየ የምወተውትህም በዚህ ምክንያት ነው። (ገጽ 22)

4.4 የእኔ ጥያቄ ግን የጥፋትና የአጥፊወች ሞዴል የሆኑት ልጆችህ ያልነበረህን ስምና ግብር እያሰጡህ ስለሆነ እባክህ የአገርህንና የወገንህን ጉዳይ በጥንቃቄ እያቸው የሚል ተማጽኖ ያለበት ነው።…ይህን አባባል በማጠቃለያነት የገለጽኩልህ እናት አገርህን አጥፍተውና ከወገንህ ጋር በብዙ መልኩ አቋስለው ሊያቆራርጡህ ሥራየ ብለው ለዘመቱት የልጅ ጠላቶች ምን ያህል የመገልገያ እቃና የመግደያ መሳሪያ ሆነህ እንዳገለገልካቸው እንዲታይህ ለማድረግ ነው። (ገጽ 23)

4.5 ስለሆነም ከቤትህ ለተጫረው የችግር እሳት አንተው የማጥፊያ መፍትሄ ካልፈለግህለት በስተቀር ተዳፍኖ ውስጥ ውስጡን እየጋመ የመፈንጃ ቀኑን በመጠበቅ ላይ ስለሆነ ፈንድቶ የተቀጣጠለ እለት አንተኑ ተመልሶ የሚፈታተን ችግር መሆኑ አይቀሬ ነው። ያን ጊዜ ተጎጅው አንተ ብቻ ትሆናለህ ባልልም በአንተ ምክንያት ሁሉም ጉዳት ላይ መውደቃቸው ግን የአንተን ጉዳት እጥፍ ድርብ ሊያደርገው ይችላል። (ገጽ 24)

4.6 የትግራይን ሕዝብ አስቀድመህ እራስህን ነጻ ማውጣት አለብህ የምልህም እነዚህ ሁሉ የማይረሱ የጠላትነት ድርጊቶች በተወሱ ቁጥር ሲያሳፍርህና ሲያሸማቅቅህ እንዳይኖር በማሰብ መሆኑን በቅን ህሊና ተረዳልኝ፤ ስለዚህ እናት አገርህን ከሚታደጓት ሌሎች ወገኖችህ ጎን የሚያሰልፍ ጽኑዕ እምነት፣ ጠንክረህ እንድትቆም የሚያደርግህ የሞራል ጉልበትና የማይተሳሰር አንደበት እንዲኖርህ ከፈለግህ በጉዳዩ በብርቱ አስብበት። (ገጽ 26)

4.7 በብርቱ ማሰብ የሚገባህ ግን ለአሁኖቹ መርዘኞች ለበከሏቸው የማይድኑ በሽተኞች ልጆችህ ሳይሆን ለነገወቹ ንጹህ ተተኪ ልጆችህ ነው። **ማሰብ ሲባል ደግሞ በጎ ማስብ ብቻ ሳይሆን ሳያሳስባቸው መኖር የሚችሉበት መልካም ስም ማትረፍና ንጹህ ሥራ ሠርቶ ማለፍ ነው። (ገጽ27)** …እኔ እንደሚገባኝ ለሰው ልጅ የማይበገር ጠንካራው የመከላከያው ምሺግ የሰላም ሰው ሆኖ የሰላም አጥር ማጠር እንጅ በሰላም የሚኖረውን



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

> ሕዝብ በጦርነት ጨርሸ እኔ ብቻ ሰላም አግኝቸ እኖራለሁ ማለት የሥራ ለሠሪውንና የእሾህ ለአጣሪውን ዳፋ በውል አለመረዳት ነው፣ (ገጽ 28)...ወዘተ የሚል ነበር።

በአጠቃላይ ጽሑፉ ከላይ ባጭሩ በጠቃቀስኳቸው ጥያቄወችና ማሳሰቢያወች ላይ ከማትኮር ባለፈ ሌላ ዓላማም ሆነ ከሥርዓት የወጣ አባባል አልነበረውም። የትግራይን ሕዝብ ሊቃሎ የሚያይና በዘር ጥላቻ ላይ የተመሠረተም አልነበረም። በተለይም ከኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ሆኖ የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ ጥሪ የሚያቀርብ እንጅ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር ለማለያየትና የትግራይን ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ለመነጠል በታለመ እቅድ ላይ የተመሠርተም አልነበረም። ወያኔወች ከሚያመጡብህ ባለብዙ ፈርጅ ችግር እራስህን ነጻ ማውጣት አለብህ ከሚል ተማጽኖ ባለፈ አብረህ ትጨፈለቃለህ የሚል ማስጠንቀቂያም የለበትም። ስለዚህ ጠቃሚ እንጅ ጎጅ ጎን አልነበረውም። ነገር ግን የእኔን ጠቃሚ ሐሳብና የጋራ መፍትሄ ማፈላለጊያ ስልት አስተካክሎ ለማየት በማይችል የተበከለ አመለካከት አይተው ምን ያህል አዛብተው እንደተረጎሙትና የእነሱ እምነትና ግብር ታሪክ ግልባጭ አድርገው እንዳቀረቡት የዶክተር አረጋዊ አባባሎች በቂ ማረጋገጫወች ይመስሉኛል። ለመልካም ሥራ ያልታደለው አዕምሮዋቸው ባይረዳውም ከእኔ በግልጽ ከቀረበ ጥያቄ ይልቅ የትግራይን ሕዝብ በብዙ ጎኑ የሚጎዳውና ለውርደት የሚዳርገው ግን በኢትዮጵያዊነቱ ሲያገኝ የኖረውን ሁለንተናዊ ሐብትና ክብር በማሳጣት በልዩ ገነት የሚኖር ልዩ ፍጡር አድርጎ ለማሳየት ሲሉ እነሱ በማደረግ ላይ ያሉት ርብርቦሽ ነው።

## ለ. 2. <u>ጥያቄወቹ ያስገኙት ውጤት፣</u>

እንደ እኔ ግምጋሜ ጽሑፌ የተመሠረተባቸው አራቱም ጥያቄወች ተደጋግፈው ጠቃሚ ውጤት ያሏቸው ለውጦችን አስገኝተዋል የሚል እምነት አለኝ። ይህን ስል የትግራይ ሕዝብ ተጨባጭ ለውጥ አሳይቷል ለማለት አይደለም። ጠቃሚ ለውጥና ውጤት አስገኝተውል ከሚያሰኝ ግምጋሜ ላይ ያደረሰኝ በአንድ በኩል የማጥፊያ መሳሪያ አድርገው የሚገለገሉበት የትግራይ ሕዝብ እነሱ እንደሚሉት ከተጠያቂነት ነጻ የሆነና በልማቱ ያልተጠቀመ ሳይሆን ከመነሻው ጀምሮ ከጎናቸው ያልተለየና በማንኛውም መልኩ አብሮ የተዘፈቀበት መሆኑን ደህና አድርገን እንደምናውቅ በግልጽ ማሳወቃችን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የአንድነቱ ኃይል 20 ዓመት ሙሉ ፋይዳ በሌለው ይሉኝታ ተሸፋፍኖና በሰፊ ትዕግስት ታምቆ የኖረውን በትግራይ ሕዝብ ምክንያት የመጣ ሁለንተናዊ ህልውናን የማጣት ጥያቄ በይፋ አውጥቶ እየተወያየበት መሆኑ ነው። ከዚህ በኋል የሚቀረው ቢኖር ፍርዱን ለተገፋ ይበል ብሎ መነሳት ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት ለሚደርሰው ጥፋትና እልቂትም በሞራልም ሆነ በታሪክ ተጠያቂ ሊያደርገው የሚችል ምንም ነገር እንደሌለ መተላለቅን ያለአማራጭ ያቀረቡልን ወገኖች በውል ሊያስቡበት ይገባል።

ጥያቄዎቹን በዝርዝር ለማየት ግን፣ ለመጀመሪያው ጥያቄ የወያኔወች የደጀን ኃይል፣ የዘረኝነት በሽታ ለሰበረው ስማቸው ጠጋኝ ወጌሻና የውበት ቀለም ቀቢ የሆኑት ዶክተር በተለዋጭ የድርጅት ስም ብቅ ቢሉም ከመነሻው ጀምሮ አብረው ሲያካሂዱ የኖሩት ገሐድ እውነታ በመሆኑ ለትግራይ ሕዝብ አልተደረገለትም ብለው አላስተባበሉም። ለመከላከል የሞከሩት ግን እሳቸው የመሠረቱት የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ሰወች ያን ሁሉ የሚያደርጉት በመንግሥትነታቸው እንጅ በዘረኝነት ተገፋፍተው አይደልም የሚል ነው። ክምን አኳያ እንዳደርጉት ምስክርነቱን መተው የነበረባቸው ግን ለተጎጅው ሕዝብ እንጅ ሁሉንም እኛው ብቻ ለእኛው ብቻ እንሁንበት ለሚሉት ሁለንተናዊ ወጀለኞች አልነበረም።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ከአንደኛው ጥያቄ ጋር ተደጋጋፊ ለሆኑት ለሦስተኛውና አራተኛው ጥያቄዎችም ዶክተሩ የትግራይን ሕዝብ ወክለው መልስ ሰጥተውባቸዋል። መልሳቸውም "ጄኔ/ ኃይሌና የአመልካከት ተጋሪወቻቸው ጥሪያቸው አዎንታዊ ምላሽ ማግኘት የሚችሉት ግን ራሳቸውን ከዘር ጥላቻ አባዜ ነጻ ሲያወጡ ነው። የዘር ጥላቻ የተጠናወታቸው ወገኖች የትግል ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ አለማግኘቱ ግን አግባብ ነው። ለወደፊቱም ቢሆን ከማንም ህዝብ አዎንታዊ ምላሽ አያገኙም" የሚል ነው። (ገጽ9) ይህ አባባል የጥያቄው ባለቤት ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብና ጥያቄው ለያዘው መልዕክት ሳይሆን መልዕክቱን ላደረስኩት ለእኔ ብቻ በማስመሰል የተጻፈ ነው። እንዲህ ያለው ሽፍጥ ለትግራይ ሕዝብ ምን ያህል ዘለቄታዊ ውጤት እንደሚያስገኝለት ግን ወደፊት የሚታይ ስለሆነ ለምስክርነት አልቸኩልም። በመሠረቱ ጥያቄው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ነው። ዓላማውም የማስመሰያ ምክንያት የሚደረደሩበት ሳይሆን አንድ ሁነኛ መልስ ብቻ የሚፈልግ ነው። **እሱም ልጆችህ የሁላችንም የሆነችውን እናት አገር እያጠፉብንና እኛንም ሰላም እየነሱን ስለሆነ በጥፋቷ ብቸኛ ተጠቃሚ ሆነህና ችግሩ የማይመለከትህ ተመልካች መስለህ ከምትታይ ይልቅ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ ተባብረን ልናድናት ይገባል የሚል ነው።** ይኸም ማለት ለራሱ ኢትዮጵያዊነት ሲል መወጣት የሚገባውን ግዴታ እንዲወጣ ከማሳሰብ ባለፈ ለእኔ ስትል ይህን አድርግልኝ የሚል ተማጽኖ የለበትም። ከዚህ ውጭ ብዙ አጋጣሚወች ተጋግዘው በፈጠሩት ጊዜያዊ ለውጥ ምክንያት አንዱ ከራሱ በላይ ሆኖ ተጠያቂ የሚሆንበት ሌላው እራሱን ጥሎ ጠያቂ መስሎ ተሚታይበት አጋጣሚም እንዳልሆነ የዘረኝነት ኩፍኝ ካይናቸው ላይ ለጣለባቸው ዶክተር አልታያቸውም። ለዚህ መሠረታዊ ጥያቄ መልሱ ሲታጣና ማጠፊያው ሲያጥር በተበከለ ዓይን ሁሉንም እንደራሳቸው አድርገው እያዩ ዘረኛ ብሎ መፈረጅ ግን በንጹሐን ደም የተበከለ ታሪካቸውን የሚያነጻና ሲቆለል ከኖረው የተጠያቂነት እዳ አይቀንስም። የትግራይ ሕዝብ ግን እንደእስካሁኑ በይሁንታም ይሁን በዝምታው ከቀጠለ በኢትዮጵያዊነቱ ላይ እንደወሰነ ስለሚቆጠር ሌላ የእቅድ ማሟያ ጊዜና የማስታመሚያ ጥያቄም ሆነ ጠያቂወች እንደማይኖሩ በሁላችንም ዘንድ ግንዛቤው ሊኖሮ ይገባል።

ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ ከጠበቅሁት በላይ ስኬታማ ሆኖዋል የሚል ግምጋሜ አለኝ። ጽሑፌ በልዩ ልዩ ድረ-ገጾች ወጥቶ ለንባብ የበቃ ከመሆኑ በተጨማሪ የመልዕክቱ ዓላማ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ በተለይ በኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች የመወያያ መድረክ ደጋግሞ እንደተነበበና ሰፊ ውይይት እንደተደረገበትም ተከታትያለሁ። የኢትዮጵያ ችግር ምንጭና ማድረቂያው የትግል ስልት የትና ምን መሆን እንዳለበት ጠንቅቀው በሚያውቁ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ከተነገሩት በርካታ ገንቢ አስተያየቶች ውስጥ አንድ ወንድሜ የተናገረውን በዋቢነት ብጠቅስ "**ጄ/ኃይሌ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ላይ ቤንዝን ነው ያርከፈከፉበት**" ያለውን አስታውሳለሁ። ሌላዋ እህቴም "**እስከ አሁን ድረስ ይህን ችግር በግልጽ እንዳንናገር ተከልክለንና አፋችን ታፍኖ ነበር። ከዛሬ ጀምሮ ግን ጄኔ/ ኃይሌ (ያውም ከምርቃት ጋር) ታፍኖ የኖረውን አንደበታችንን ስለከፈቱልን ካሁን በኋላ ማንም ሊከለክለን የሚችል የለም**" ያለችውንም አስታውሳለሁ። የዶክተሩን የጭንቀት ጩኸት ከሁለቱም ወገኖቸ ግምጋሜ ጋር አዛምጀ ሳገናዝበው አስተያየታቸውን አደንቃለሁ። ያደነቅኋቸውም ጽሑፉን በቀና መንፈስ ስለተረጎሙልኝ ሳይሆን ግምጋሜያቸው ጽሑፉ ያካተታቸውን ሁለንተናዊ መልዕክቶች ያገናዘበ በመሆኑ ነው። በእርግጥም ወንድሜና እህቴ ከብዙ ነገሮች ጋር አገናዝበው እንደተረጎሙት ይኸውና በአሁኑ ወቅት ብዙወቹ ኢትዮጵያውያን በልባቸው አምቀው ይዘው እያብሰለሰሉ አጋጣሚ ሲጠብቁለት የኖሩትን የትግራይ ሕዝብ በዝምታ ጋርዶ ይዞት የኖረውን ድብብቆሽ ይፋ አውጥቶ በሰፊው እየተነጋገረበት ነው። የውይይቱ ማዕከል ያደረገው ፍሬ ሐሳብ በአንተ ምክንያት የመጣው ባለብዙ ፈርጅ ችግር እናት አገራችንን እያጠፋብንና እኛንም መኖሪያ ቀርቶ መቀበሪያ አፈር እያሳጣን ስለሆነ ግፍና በደሉ ሞልቶ ከመፍሰሱና አንተንም አብሮ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ወደሚያጥለቀልቅ ማዕበል ከመለወጡ በፊት ልታስቆመው ይገባል የሚል ቁርጠኛ አቋም የያዘበት ነው። የጽሑፉን ሕዝባዊ ተቀባይነት ዶክተር አረጋዊ ቢሆኑም አልካዱም። ለማስመሰል የሞከሩት ግን "ጀኔራሉ በደርግ ጊዜ በአገራችን የሥልጣን እርከን ውስጥ ከነበራቸው ቦታ አንጻር ጽሁፉ ሲመዘን በርካታ ወገኖቻችንን በጥላቻ መንፈስ ሊበክል የሚችል ሆኖ ስላገኘነው ነው፡" ይላል። እኔም የፈለግሁት እንዲዚያ ያለ ሕዝባዊ ተቀባይነት እንዲኖረው ነበር፤ እየሆነም ነው።

"የባህር ዳር ሲታረስ የጓጉንቸሮች ሆድ ይጮህል" እንደሚባለው ጽሑፉ በሕዝቡ ትግል ላይ ያርከፈከፈው ቤንዚንና የጫረው እሳት እየጋመና እየተቀጣጠለ መጥቶ የዘረኞቹን ምሽግ የዶግ አመድ ማድረጊያው ጊዜ የመቃረቡ መርዶ ለዶክተሩ ድብቅ አልሆነም። የውር ድንብስ ጩኸታቸው ሐቅም ከዚህ የመነጨ ነው። በኢትዮጵያ ሕዝብ የተጠላ ነው የሚሉት ደርግ ባለሥልጣን የነበረ ሰው ያወጣው ጽሑፍ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አለው ብሎ መመስከር ግን በትግራይ ሕዝብ ላይ ለመመስከር የሚያስችል የሞራል ብቃት የለውም ብለው ከቀሳፈጡት ጋር የሚጣረስ በመሆኑ ሰውየው አንድም የሚሠሩትን ለይተው የማያውቁ፣ አለያም ለምስክርነት የማያበቃ የአዕምሮ ችግር እንዳለባቸው የሚያመለክት ይመስላል። ስለዚህ አገር አጥፊና ትውልድ ገዳይ የሆኑት ቅጥረኛ ከሐዲወች እራሳቸውን ከማይቀርላቸው የተጠያቂነት እዳ ለመከላከል ሲሉ **"ነፍጠኞችና ጽንፈኞች"** እያሉ ቢጯጯሁም ጽሑፉ ግን ሕዝቡንና ሕዝባዊ ትግሉን እጅ ለእጅ በማጨባበጥ በእምነትም ሆነ በተግባር ተዋህደው እንዲዘምቱ ያነሳሳ በመሆኑ ካሁን በኋላ ወደፊት እንጅ ወደኋላ የሚልላቸው እንደማይኖር ቁርጣቸውን ሊያውቁት ይገባል።

## ለ. 3 <u>የዶክተር ዐረጋዊ የማስመሰያ ትርጉም፣</u>

"የኋልዮሽ ጉዞ አገራችንን ይበትናታል" የሚሉን እነማን ናቸው? ምን አቅደው የተነሱና ሲያደርጉስ የኖሩ ናቸው? የሚሉትን ጥያቄወች ሰፋ አድርጎ ማየት አስፈላጊ መሆኑን ቀደም ሲል ጥቅሻለሁ። ከዚህ መሠረተ ሐሳብ በመነሳት በመጀመሪያ ዶ/ር አረጋዊ በረሄ የማሌሊትን ህዋስ ደደቢት ውስጥ ከጸነሱበት ጊዜ ጀምሮ በፈጠሩት ድርጅታቸው ተጨንግፈው እስከወጡበት (እትብታቸው ባይቆረጥም) የማሌሊት ምሥረታ ድረስ የቀጠለ ፖለቲካዊ ህይወታቸውን እንመልከት። በመሠረቱ ዶ/ር አረጋዊ በረሄን በአካል ባላውቃቸውም ከስማቸው ግዝፈት (አረጋዊ) በመነሳት በትልቁ የሚያስቡ ትልቅ ሰው ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት ነበረኝ። ለካስ ህጻን ወይም አዕምሮውን እንደሳተ ሰው በሽተኛ ሰው ትላንት ያደረጉትን መለስ ብለው ማገናዘብ የማይችሉ ሰው መሆናቸውን የተረዳኋቸው እጅና እግሩን ካጣ ውልየለሽ ጽሁፋቸው ነው። ምናልባትም የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት በትንሹ የሚያስቡ ትንሾች መጠራቀሚ ሆኖ የቀረው በእሳቸው ልክ እየተመጠኑ ስለገቡበት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለኝ። ተጨንግፈው እንዲወጡ የተደረጉበትም በዚሁ ትንሽነታቸው ሳይሆን አይቀርም። ስለሆነም አንባቢዎች የኔን ያህል እንዲረዱቸውና የራሳቸውን የህሊና ግምት እንዲያሳድሩ በማሰብ ከብዙወቹ የራሳቸውን ማንነት እንደ ስጦ አጋልጠው ካሳዩበት የማስመሰያ ቅቦች አንዳንዶቹን ለዋቢነት ያህል ጠቅሻለሁ።

***አረጋዊ በረሄ በአቶነታቸው ዘመን ከማሌሊት ግንባር ቀደም መሥራቾች አንዱ የሆኑ፣ የመሠረቱት ድርጅት መሪና ያደራጁት ጦር አዛዥ ሆነው ለብዙ ዓመታት የመሩ ከወያኔወች የመጀመሪያው ሰው ናቸው። በእነዚህም ድርብርብ ሐላፊነታቸው፣ የዘረኝነት መጠንሰሻ ጋኑን ደደቢት ጫካ ውስጥ ቀድመው የተከሉና የመበከያ መርዙን ጠንስሰው የጠመቁ፣ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ከ100 ዓመት በፊት አልነበረችም ብለው ሽምጥጠው የካዱና ብሔራዊ አንድነቷን ለማናጋት ያስችለናል ያሉትን እቅድ ነድፈው ያጸደቁ፣ ለቤተ-ሙከራቸው ይረዳ ዘንድ በመጀመሪያ ኤርትራን ለማስገንጠል 65000 ጦር አዝምተው የቀይ ኮከብ ዘመቻን ያከሸፉና ያስገነጠሉ፣ አቅደው ለተነሱበት ዓላማ መሳካት ተቃዋሚ ይሆንብናል ያሉትን የአማራውን ሕዝብ በቅድሚያ ለመጨረስ የመጀመሪያው***



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

**ዒላማቸው አድርገው የዘመቱ፣ የእነዚህ ሁሉ እልቂትና ውድመት ባዳበረው የድል ማሳ ላይ ታላቅ የትግራይ ሪፐብሊክ አገር ለመገንባት ግባቸው አድርገው የተነሱ፣ በአጠቃላይም በወንድማማችነት ፍቅር እየተሳሰበ የኖረውን የአንዲት እናት አገር ሕዝብ በዘር ፖለቲካ በክለው እርስ በርሱ ለማፋጀት የትግል ስልታቸው አካል አድርገው የዘመቱ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ቀንደኛ ጠላት ከሆኑት አንዱ ናቸው። በአሁኑ ወቅት አገሪቱን በማጥፋትና ሕዝቧን በመጨረስ ላይ ያለው የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት የሚመራው ማሌሊት ከመነሻው የዓላማው መገንቢያ መሠረት አድርጎ በጣላቸውና የትግሉ ማስፈጸሚያ ስልት የማዕዘን ድንጋይ አድርጎ ባቆማቸው የማፍረሻ ቀመሮች ላይ ተመሥርቶ ነው። በመሆኑም የአረጋዊ በረሄ ከደደቢት እርቆ መኖርና በተለዋጭ ስም ብቅ ማለት ከእነዚህ ሁሉ የክህደት ወንጀሎች እንዲርቁም ሆን እንዲደበቁ አያደርግም።**

እንግዲህ **"የኋልዮሽ ጉዞ አገራችንን ይበትናታል፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ያለውን ስር የሰደደ የአንድነትና የመተሳሰብ ትስስር ለመበጠስ የተደረገ አደገኛ እንቅስቃሴ ነው"** ወዘተ እያሉ አዘውትረው ሊያታልሉን የሚፈልጉት በዚህ ዓይነቱ የቃላት ቀለም ቀቢነትና የማስመሰያ ኢትዮጵያዊ ተቆርቋሪነት ነው። እንግዲያውማ የዘመናት ታሪክን ክዶና በብሔራዊ ደረጃ የተቀመጡበትን ስምና ክብር አዋርዶ እንደ ግመል ሽንት ወደኋላ እየተንጠባጠቡ በመሄድ በመንደር ጉሮኖ ውስጥ ከመመሸግ የዘቀጠ ምን የኋልዮሽ ጉዞ አለ? የእናት አገርን ብሔራዊ አንድነት ከማናጋትና የባህር በሯን ከመዝጋት፣ ማህልና ዳር ሳይለዩ እየከለሉ ከመስጠትና እያጫረቱ ከመሸጥ የባሰስ ምን አገርን የመበታተን ብቻም ሳይሆን ጨርሶ የማጥፋት ዘመቻ አለ? ከአገሪቱ 1/3 የሚሆነውን የአማራውን ሕዝብ (ያውም እነርሱ ገድለውም ሆነ ወይም ለመሠሪ ፖለቲካቸው ሲሉ ሆን ብለው የቀነሱትን 2.4 ሞሊዮን ሕዝብ ሳይጨምር) በጠላትነት ፈርጆ ጨርሶ ለማጥፋት አቅዶ ከመነሳትና ተደራጅቶ ከመዝመት፣ ቁጥሩ በማነሱ ምክንያት በተ/መንግሥታት ጥበቃ ስር ያለውን የአኙዋክን ሕዝብ ለማጥፋት ከሚኖርበት አካባቢ ድረስ ሄዶ ትውልድ የማይረሳው ዘግናኝ እልቂት በመፈጸም ስር የሰደደ የሕዝብ ትስስርን ከስሩ ነቅሎ የሚያደርቅ ዘመቻ በየፈርጁ ከማካሄድ የከፋና የከረፋ ምን አረመኔያዊ ድርጊት አለ? ምንስ አንጀት የሚቆርጥና ጨርሶ የሚያቆራርጥ የለየለት የጠላትነት ድርጊት አለ?

በአጠቃላይ ወልዳ ባሳደገች እናት አገርና ተዋልዶ በተዛመደ ወገን ላይ የተፈጸመው እንዲህ ያለው ክህደትና እልቂት በኢትዮጵያ ቀርቶ በዓለም የዘመናት ታሪክ እንኳ ፈጽሞ አልተደረገም፤ ወደፊትም አይደረግም። የመጀመሪያወቹ ወያኔዎች ብቻ እንደሆኑት ሁሉ የመጨረሻወቹም እነሱ ብቻ እንደሚሆኑ እርግጠኛ ነኝ። ወደ ሮሜ ሰዎች ም.3፡9 **"ሰው ሁሉ ሐጢአተኛ ነው፤ አንድ እንኳ ጻድቅ የለም፤ አስተዋይም የለም"** የሚል መንፈሳዊ መልዕት እናገኛለን። አዎ! ሰው ሁሉ ሐጢአተኛ ነው። የወያኔዎች ሁለንተናዊ ባህሪይና ድርጊት ሲታይ ግን እንደሌሎቻችን ሐጢአት የሚሠሩ ሳይሆኑ ሐጢአት ሆነው የተፈጠሩ ናችው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በክህደት ተጠምቀው የክህደት አጥማቂ የሆኑት ወያኔዎች ቀርቶ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቁ ናቸው የተባለላቸው መንፈሳዊ አባቶች ሳይቀሩ ታቦት የሚያህል ክብ ቆብ ደፍተውና ሰፊ ቀሚስ አንሰርትተው፣ ረጅም ጺማቸውን አንዠርቅቀውና ግማደ መስቀልን ያህል ቅዱስ ነገር አስረው በመንበረ ሥልጣናቸው ላይ ከተቀመጡ በኋላ ምን በማድረግ ላይ እንዳሉ ልቦናን የሚመረምረው አምላክ ፍርድ ይስጥበት ከማለት ባለፈ በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ውስጥ በመፈፀም ላይ ስላለው ብልሹ ድርጊት ዝርዝር ውስጥ ገብቼ መተንተን አልፈልግም። ኢትዮጵያዊ ኃላፊነት ከሚሰማቸው ጥቂቶች በስተቀር ልጆቻችን ስለሆኑ ተዋቸው እያሉ በጅምራቸው እንዲቀጥሉ የሚገፋፉ እንጅ "ኧረ ይኸ ነገር መጀመሪያውም ሆን መጨረሻው ለትውልድ አይበጅም" ብለው የመከሩም ሆነ ያዘከሩ ሽማግሌዎችና መንፈሳዊ አባቶች እንኳ በመካከላቸው አልተገኙም። እንዲያውም በዳዊት መዝሙር



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

137፣7፣ እንደተገለጸው “እግዚአብሔር ሆይ! ኢየሩሳሌም በተያዘችበት ቀን ኤዶማውያን ያደረጉትን አስብ፣ እስከ መሠረትዋ አፈራርሳችሁ ጣሉአት! እያሉ መጮሃቸውንም አስታውስ።” የሚለውን በእስራኤል ላይ የተፈመ ድርጊት የኢትዮጵያ ኤዶማውያንም በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊያን ላይ እያዋሉት ነው። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን ከመሠረቷ አፈራርሶ ለማጥፋትና ሕዝቧን ተመልሶ እንዳያንሰራራ ለማድረግ በሚያስችላቸው ፍርስራሽ ውስጥ አደላድለው ለመቅበር ማን እራሱን አዘጋጅቶ ያልዘመተ ወያኔና አጃቢ፣ ማንስ ክራር እየመታና ከብሮ እየደለቀ ያልፈከረና ያልጨፈረ፣ሰልፍ እየወጣም ያላጀበና ያላስተጋባ ካድሬና ደጋፊ አለ! ማንስ ነጋሪት እየጎሰመ፣ መቋሚያና ጽናጽል ይዞ እየዘመመ ያልዘመረና አብሮ ያልዘመመ ቄስና ዲያቆን ወዘተ አለ? ባጭሩ ከዚህ ሁሉ ሠልፈኛ ውስጥ ለእኛ ከዚህ ወዲያ ያሉት አብረው የዘመቱ ኤዶማውያን አይደሉም ብለን ለመለየት ይከብደናል። እነሱ ግን እርስ በርሳቸው ስለሚተዋወቁ እነዚህ ከእኛ ጋር ያልወገኑ ገለልተኞች ናቸው ብለው አስምረው ቢለዩልን ደስ ይለናል። እኛም ከእነዚያ ጋር እጅ ለእጅ ተጨባብጠን የጋራ የሆነችውን እናት አገር ለማዳን ዝግጁ ነን። ወያኔዎች ግን ይህን ሁሉ በማድረግ ላይ ያሉት እውን ከሌሎቹ የበለጠ በደል ደርሶባቸው ሳይሆን ከሌሎቹ ሁሉ እንበልጣለንና የበለጠም እንጠቀማለን ብለው በፈጠሩት በክህደት የታጀበ ሁለንተናዊ ምስቅልቅል ነውታዲያ ይኸን ሁሉ ያደረጉ የመልካም ሥራ ድሐዎች የእኛን እምነት መዋስና የእኛን እናት አገር መውረስ ይቻላቸዋልን? እንደገባኝ የወያኔዎች የውጭ ተጠሪ በተለዋጭ ስም ብቅ እያሉ የማስመሰያ ቀለም ስለቀባቡ ብቻ ከእነዚህ ሁሉ አገር የማጥፋት ወንጀልና በቀላሉ የማይለቅና የማይደርቅ የደም እዳ አመልጣለሁ የሚል ተስፋ ያላቸው ይመስላል። ይሁን እንጅ የሰው ልጅ ከአዳምና ሔዋን ሐጢአትን እንደወረሰ ሁሉ ከእነሱም አልፎ ቤተሰቦቻቸው ሁሉ የክህደት እዳቸው ወራሽ ሆነው ሲጠየቁበት እንደሚኖሩ ግልጽ ሊሆንላቸው ይገባል። ያሳማሩ መስሏቸው ማበላሸቱን ያዘወተሩት ዶክተር ”የህዝቦች ጥያቄ በቅጡ እስካልተመለሰ ድረስ ትግል ያቆማል ብሎ መገመት ጅልነት ይሆናል” ብለው ነበር። አዎ! ጅልነት ነው። ነገር ግን ጅልነቱ በዚህ የሚያመልኩና የሚመኩትን የራሳቸውን ፋሽታዊ ባህሪይ የሚገልጽ ሲሆን፣ የማይቆም ትግሉና የማይቀር ድሉ ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚመለከት መሆኑን ሊረዱት ይገባል።

ከዚህ ቀጥሎ ዶክተሩ ተጠልለው ብቅ ያሉበትን ተለዋጭ መጠሪያ ስም እንመልከት። እንደሚታወቀው የፖለቲካ ድርጅት ቀርቶ የግለሰብ ስም እንኳ የሚወጣው የወደፊት እምነትና ግብሩ መግለጫ ይሆናል ተብሎ ተገናዝቦ ነው። ከዚህ አንጻር የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ትዴት) ማለት በተለያየ ስም ከሚጠሩት የትግራይ ሕዝብ ድርጅቶች ማለትም፣ የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት፣ የትግራይ ሶሊዳሪቲ፣ ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር፣ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ሁሉንም አንድ አድርጌ ማደራጀትና ማሰለፍ አለብኝ ብሎ ከተነሳው አረና ትግራይ ጋር ግንባር በመፍጠር ትግራይን ለነጻነትና ለሉአላዊነት የሚያበቃ መሆኑ ገላጭ የሆነው የማያሻማ የስሙ ትርጉም ያረጋገጠው ሐቅ ይመስለኛል። "**የጠላ ጥንስስ የተጠነሰሰ እለት የተገዛ ጦር ቢወረውሩት ሄዶ የሚያርፈው ከድፍድፍ ጋን ላይ ነው**" እንደሚባለው የእነዚህ ሁሉ ድርጅቶች ስምና ትርጉምም ሆነ ዓላማና ግብ ተጠቃሎ ሲታይ ለዚያው ለተጠነሰሱበት መንደራቸውና ለጠንሳሾቹ መንደርተኞች እንጅ ሁላችንም በጋራ ቁመን ልንመክትላት ለሚገባን እናት አገር የሚወረወር ጦር ቀርቶ መደገፊያ የምትሆን ትንሽ ጠጠርና ለኢትዮጵያዊነት የሚስማማ ጣምና ትርጉም ፈጽሞ የላቸውም። እንግዲህ ምንም ዓይነት ብሔራዊ ዓላማና ሐገራዊ ራዕይ የሌላቸው የመንደርተኞች ስብስብ አገራችንን ለመበታተን አትዝመቱብን የሚሉን እቅዳችንን አሟልተን ለግባችን እስከምንበቃ ድረስ ጊዜ ስጡን ለማለት ካልሆነ በስተቀ እውን ከእነሱ የማይጠበቅ ጠቃሚ ነገር የሚወጣቸው ሆኖ አይደለም። የኔ ጽሑፍ ዓላማና የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ መወጣት



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ከሚገባው ግዴታ አኳያ ያቀረብኩለት ጥይቄወች ምን እንደነበሩ ቀደም ሲል በአጭሩ አመላክቻለሁ። ክህደት ያወራቸው ዘረኞች ግን የጽሑፉን መልዕክት አንብበው ለመረዳትም ሆነ ገሀድ እውነታወችን አምነው ለመቀበል ፍላጎቱም ሆነ ትግዕስቱ እንደማይኖራቸው አስቀድሞም ቢሆን የታወቀ ነበር። ስለሆነም ዶክተር አረጋዊ ምን ብለው እንደተረጎሙት ማስመሰሉን ብቻም ሳይሆን መስሎ መታየቱን እንኳ ያላወቁበትን ስመ ተቆርቋሪ ማንነት ማወቅ የሚያስችሉ ዋቢ መረጃወችን በአጭሩ ከዚህ ቀጥሎ ጠቅሻለሁ።

*"የአገራችን የፖለቲካ መድረክ እነዚህ ጽንፈኞች እንዳይቆጣጠሩትና ከምን ጊዜውም የከፋ የአገር መበታተንና የወገን መተላለቅ እንዳይከተል...በዚህ መንገድ ህዝብን ከህዝብ ለማባላት የሚፍጨረጭሩትን ጽንፈኞች በቀላሉ ማግለልና እርቃናቸውን ማስቀረት...ከሁሉም የተውጣጣ አምባ ገነን ገዥ መደብ እያለ ሕዝብን ከፖለቲካ ድርጅት ሳይለዩ እንደ ሕዝብ በጠላትነት ፈርጀው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች እየተበራከቱ በመምጣታቸው...በአሁኑ ሰዓት የትግራይን ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ለመነጠል እየተደረገ ስላለው አደገኛ እንቅስቃሴ..(ገጽ1)*

*-አንዳንድ ሐላፊነት የማይሰማቸው ጭፍን አክራሪወች እንደሚያራግቡት የትግራይን ሕዝብ ከተቀረው የኢትይዮጵያ ሕዝብ የተለየ መንፈስ ያደረበትና ከህወሐት/ኢህዴግ ጋር በፕሮግራምና በዓላማ ተሳስሮ የሚጓዝ እንደሆነ...የትግራይ ህዝብ በእምነትም በዓላማም አንድ ሊሆኑ አይችሉም፣ ሆኖውም አያውቁም።* (ግጽ2)

*-የትግራይን ሕዝብ ሞራል ለመንካትና በሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ እንዲጠላ ለማድረግ ሲካሄድ የቆየውና አሁንም ፍጥነት፣ ጥልቀትና ስፋት ተሰጥቶት በመሰራጨት ላይ ያለው መርዘኛ የጽንፈኞች ፕሮፓጋንዳ...በእጅጉ የሚያሳዝነው ግን..የቀድሞ የኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ኃይል አባል የነበሩ ብ/ጄኔራል ኃይሌ መለሰ በፈቃዳቸው የዚህ የከረፋና አገር አፍራሽ የጥላቻ አራማጆች ካምፕ መቀላቀላቸው ነው። (ገጽ3) -በዚህ ጽሁፋቸው ውስጥ ጀኔራል ኃይሌ የትግራይ ሕዝብና ህወሓት በአንድ ሙቀጫ ውስጥ ከተው ፈጭቷል። በህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ ሥር የሚማቅቀውን የትግራይን ህዝብ ከአምባገነኑ የህወሓት አመራር ጋር አዳብለው ለመጨፍለቅ ከመሞከር አልታቀቡም። (ግጽ4) - እነዚህ ሁለት ጥቅሶችን ስንምስለከት ጀኔራሉ የትግራይ ሕዝብ ተሸክሞት ያለ ፍዳ ምን እንደሆነ እንደሚያውቁ፣ ግን በምን ቸገረኝነት የትግራይን ህዝብ ለማንኳሰስ እንደተነሳሱ ግንዛቤ እናገኛለን። (ገጽ5)*

*-ጀኔራል! እርሶና መሰሎቻዎ ከህወሐት/ኢህአዴግ ጋር የይዘትም ሆነ የዓይነት ልዩነት የላቹህም።..እርስዎ በአቋም ደረጃ የሚያራምዱት የህወሓት/ኢህአዴግን አቋም በመሆኑ የሚያጣላቹህ ሥልጣን ብቻ እንደሆነ ጽሑፍዎ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። (ገጽ6) "በትግሬነታቸው የተገደሉ ቀርቶ ታስረው የተንገላቱ አንድም እንኳ ለማስረጃ ያህል አይገኝም"ሲሉ በዘሩ የሚገደልና ታስሮ የሚንገላታ ወገን አለ ለማለት የቃጣቸው ይመስላል። (ገጽ8).. -በአንዳንድ የህወሓት ዓላማ አራማጆች ባለቤትነት በሚንቀሳቀሱ ድረገፆችና ብሎጎች ላይ የሚታዩ የዘር ጥላቻን የሚያራግቡ ፅሑፎችና ፀሓፊዎንም አጥብቀው እንደሚኮንኑና እንድሚታገሏቸው ይገልጹና የህወሓት ደጋፊወች ቢያደርጉት ግን ዓላማቸው ነውና የሚገርመን አይሆንም ይሉናል። (ገጽ10)*

*-ጀኔራል ኃይሌ ባቀረቡት ባለ28 ገጽ ፅሑፍ...አጠቃላይ መልእክቱ የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ በሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ እንዲጠላ ለማድረግ ያለመ በመሆኑ...ህዝብን እንድህዝብ ለማስጠላትና ከወገኑ ለመነጠል የሚደረገው ሙከራ ሊያስከትለው የሚችለው ጠንቅ ከወዲሁ መገንዘቡ አገራችንን ከውድቀት ያድናታል ብለን እናምናለን።...ነገ ህወሓት/ኢህአዴግ ተወግዶ እነዚህ ዓይነቶቹ ጽንፈኞች ሥልጣን ቢይዙ ኢትዮጵያ የሚደላትና ትግል የሚያቆም የሚመስላቸው ወገኖች ካሉ እጅጉን የዋሆች ናቸው። የህዝቦች ጥያቄ በቅጡ እስካልተመለሰ ድረስ ትግል ያቆማል ብሎ መገመት ጅልነት ይሆናል። (ገጽ11)*

እኔ እንደገባኝ ዶክተሩ በቃልና በቀለም የማስመስል ችግር የለባቸውም። ከማፍረስ በስተቀር የመገንባት ታድሎ ስለሌላቸው እንጅ ግንበኛ ቢሆኑ ኖሮ ጥሩ ቀለም ቀቢ ይወጣቸው ነበር።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ችግራቸው ግን የሚቀቡት ሁሉ መሆን ቀርቶ ሊመስልላቸው እንኳ አለመቻሉ ነው። ምክንያቱም አስመስላለሁ ብለው የሚቀቡት የእነሱን እምነትና ግብር ግልባጭ እንጅ ገሀድ እውነታውን ባለመሆኑ ነው። ለድህነትም ይሁን ለወገናዊነት ከማይሆን 11ገጽ ኑዛዜያቸው ውስጥ የተወሰኑትን ጠቅሻለሁ። ካስመሰሉባቸው ቃሎችና ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የትኛዎቹ በእርግጥ በኔ ጽሑፍ ውስጥ እንዳሉ አገናዝቦ የህሊና ዳኝነት የመስጠቱን ሐላፊነት የምተወው ግን ለኢትዮጵያዊያን አንባቢወች ነው። በእኔ በኩል ደግሞ እኔን የእነሱ እምነትና ግብር ወራሽ አድርገው ለማሳየት ሲሉ ከቀባቡዋቸው ውስጥ አንዳንዶቹን መለስ ብየ ማብራሪያ እንድሰጥባቸው እገደዳለሁ።

በመጀመሪያ ደረጃ እነሱ ብቻ አጠቃለው በያዙት ሥልጣን የማይቀጥሉና በሚፈልጉት የዘረፋ ስልት ማለትም ኢትዮጵያ ለትግራይ ሪፐብሊክ ግንባታ የማትነጥፍ ጥገት ሆና እስከ አልቀጠለች ድረስ የመፈራረስ አደጋ እንደሚያጋጥማትና ወያኔወች ቢወድቁ እንኳ እንደይማይደላት ደጋግመው እያስጠነቀቁን ነው። እኔ እንደሚገባኝ እንዲህ ያለውን ማስጠንቀቂያ የሚሰጡን በሁለት ምክንያቶች ነው ብየ ገምቻለሁ። የመጀመሪያው ተቃዋሚዎቻችን ሁሉ ሽባ አድርገን እኛ ብቻ በየፈርጁ የተደራጀን ስለሆነ የሚደፍረን የለም በሚያሰኝ የጥፋት ትምክህት ስላበጡ ሊሆን ይችላል፤ ነውም። ነገር ግን እብጠት የራሱ የሆነ የውልደት፣ የእድገትና የሽረት ሕግ ስለአለው ወያኔወችም ከዚህ የቅራኔ ሕግ ውጭ ስለማይሆኑ የራሳቸው እብጠት ፍንድቶ ብትንትናቸው የሚወጣበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም። ሌላው ምክንያት ለአገራችን መልካም ራዕይ የሌላቸው ሱናሜዎች ከሪፐብሊካቸው ምሥረታ በኋላ ምስቅልቅሏን ለማውጣት ያላቸውን እቅድና ሁና እንዲያዩዋት የሚፈልጉትን ምኞት መግለጻቸው ይመስለኛል። ነገር ግን ባለፉት 20 ዓመታት ያለ ብሔራዊ መንግሥትና ያለትግራይ ሕዝብ ተሳትፎ ተጠብቃ የኖረች አገር መሆኗን ሊረዱት አልቻሉም። ያውም ቃላት ሊገልጸው ከሚችለው በላይ የሆነ ሴራ እየተሸረበባትና የተቀነባበረ ዘመቻ እየተካሄደባት ማለት ነው። እንደ እነሱ እቅድና ምኞት ቢሆንማ ኖሮ ኢትዮጵያ ልትጠፋ የነበረው አርደው ለመቃረጥ ለተሳሉ ሥጋ-በል ግብረ አራዊት ለቅርጫ የቀረበችና የመበለቻ ቻርተራቸው የጸደቀ ጊዜ ነበር። ነገር ግን ልዑል እግዚአብሔር ያ እንዲሆን ስለአልፈቀደ እንደ ባቢሎን ሰዎች ግንብ መሐላቸው እንዲፈራርስና ቋንቋቸው እንዳይገጥም አድርጎ አሳይቶናል፤ ወደፊትም በበለጠ እንደሚያሳየን እምነቴ ጽኑዕ ነው። **የዘለቄታው መሠረታዊ መፍትሄ ግን እነሱ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን አጥፍተው ብቻቸውን ለመኖር የሚችሉባት አገርና ዓለም ለመገንባት እንደሚጣደፉት ሁሉ እኛ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ እንደ እነሱ የትግራይን ሕዝብ ለማጥፋት ባንዘምትም በኢትዮጵያዊነታችን ላይ የዘመቱትን ወያኔያዊ ትግሬዎች አስወግደን እነሱ የማይኖሩባት ኢትዮጵያ እንደምትኖር አድርገን ለማሳየት የሕዝባዊ ትግላችን ማዕከላዊ ግብ ሆኖ እንዲያዘምተን ማድረግ ነው። ይህ** ደግሞ የጊዜ ጉዳይ እንጅ መለስ ዜናዊም ሆነ ከማሌሊት ተጨንግፈው የወጡት ዶ/ር አረጋዊ በረሄ እንደገና ለመወለድ ደደቢት ጫካ ተመልሰው ቢገቡ እንኳ የማይቀር ሂደት መሆኑን በውል ሊረዱት ይገባል። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ በማንኛውም መልኩ እራሱን እያዘጋጀ ነው። ባለፉት ዓመታት የገበየው ስፊ ልምድም ከእሱም አልፎ ለልጅ ልጆቹ ሊወራረስ የሚችል ነው። የራሱ ድክመት ምን እንደሆነና መቸ እንደጀመረም በሚገባ አገናዝቧል። ስለዚህ አመጹን መቸ? የትና እንዴት እንደሚጀምር አካላዊና ህሊናዊ ዝግጅት አድርጎ የፈጣሪውን ፈቃድ እየተጠባበቀ ነው። በእርግጥ ይህ ሁለንተናዊ ዝግጅት በክህደት ትምክህት ለታወሩት ወያኔወች ግልጽ አይደለም። ሊሆንላቸውም አይችልም። የማይቀረው ብሔራዊ ክተት ሲታወጅ ግን፣

በጎጃም በወሎ በሸዋ በጎንደር፣

በሲዳም ባሌ ሐረርጌና አፋር፣



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ጎሙጎፋና ከፋ፣ ወለጋ ኢሉባቦር፣

በጋምቤላ አሶሳ ከማህል እስከ ዳር፣

እዚህ ያለ ብረት፣ እዚያም ያለ ብረት፣

ተነስ ታጠቅ ሲባል የተመዘዘ ዕለት፣

ዳር የቆመው ሁሉ ድብልቅልቅ ያለ እለት፣

ወይያኔ፣ ወይያኔ ወይያኔ ወዮለት።

ከዚህ የሞት ሽረት ትግል በኋላ አይቀሬው የድል ነጋሪት ሲጎሰም ከኢትዮጵያና ከእነሱ ሪፐብሊክ የማን አካል ፈርሶ የማን ጸንቶ ለዘላለም እንደሚኖር በዚያን ጊዜ ያዩታል። የዛሬው ድንፋታ ወደ አልጠብቁት ዋይታና ለቅሶ የሚለወጠውም በዚያን ጊዜ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ያን ለማድረግ ሲነሳ ደግም የአዲስ ምልስ ወያኔወችን አዝማችነት ቀርቶ አብረን እንዝመት ባይነታቸውን እንኳ አይፈልግም። ለኢትዮጵያ ቅን የማያስብ ህሊናቸው የሚያስመስልበትን የምላስ ተቆርቋሪነትም አያምንበትም። ምክንያቱም በስመ ኢትዮጵያዊነት አብረው እየኖሩና እየዘመቱ ምን ሲያደርጉ እንደኖሩ ጠንቅቆ ከማወቁ በተጨማሪ የእስካሁኑን ችግር ያልተጋሩትንና ጥሪውን ያልሰሙትን ጊዜ ፈጠር ወገን ነን ባዮች አምኖ እንደወገን ለማየት ስለሚቸገር ነው። ሰው የሚለካው በችግር ጊዜ በመሆኑ ያስቸገሩትንም ሆነ አብረው የተቸገሩለትን ጠንቅቆ ያውቃልና ነው።

ሌላው ዶክተሩ የሳሉት በኔና በዎያኔዎች መካከል የይዘትም ሆነ የዓይነት ልዩነት እንደሌለን፤ በአቋም ደረጃም የምናራምደው አንድ ዓይነት አቋም እንደሆነ ነው። ያጣላንም የሥልጣን ጥያቄ ብቻ ነው ማለታቸው ነው። በተፈጥሮ ያልታደለች መልከ ጥፉ ያጋጠማቸው አንድ ችግረኛ ሰው **“ብዙ ዓይነ ሥውሮችን አየሁ፣ እንደ አንች ከስሩ የፈለሰበት ግን አላጋጠመኝም”** አሉ ይባላል። እኔም ባለፉት 35 ዓመታት ባሳለፍኩት ፖለቲካዊ ሕይወት ከብዙ መልካም ሰወች ብዙ ጠቃሚ ትምህርትና ልምድ የገበየሁትን ያህል በእኔነቴና በዓላማየ ላይ ከመጡ ብዙ ከፍተው ከሚያከፉ ክፉ ሰዎችም ጋር ተፋልጫለሁ። ነገር ግን እንደ አረጋዊ በረሄ ያለ ያውም ብዙ ነገሮችን አንብቤ የተረዳሁና ተመራምሬ ያወቅሁ ነኝ ከሚሉ ዶክተር በሁለመናቸው የፈለሱ፣ ማየትና ማገናዘብ የተሳናቸው ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም። ሌላው ቢቀር ለራሳቸው ሲሉ በማስመሰሉ ሳያዉቁበት መቅረታቸው ለሌሎቹ ቀርቶ ለራሳቸው እንኳ የማይሆኑና ነገሮችን በወጉ መዝኖ ትክክለኛ ምውክርነት ሊሰጥ የሚችል ኅሊና የሌላቸው ለመሆኑ ሁነኛ ማረጋገጫ ነው። አልያማ የማሌሊት ግንባር ቀደም መሥራችና ለግብ የሚያበቃው ፖሊሲ ቀያሽ የሆኑት አረጋዊ በረሄ እራሳቸውን ከዚህ ሁሉ ነጻና ከወያኔዎች እሩቅ አድርገው እኔን ከወያኔዎች ጋር አንድ ናችሁ ስል የሕዝብ ህሊና ምን ያህል ይቀበለዋል ብለው እራሳቸውን ይጠይቁ ነበር። ነገር ግን ሊጠይቅም ሆነ ሊጠየቅ የሚችል ኅሊና ስለሌላቸው ለማድረግ አልቻሉም። ለነገሩ እንዲህ ያለው ችግር የሳቸው ብቻም ሳይሆን የሁሉም ወያኔዎች ችግር ስለሆነ እሳቸውን ከሠፈራቸው ውጭና ከመንደራቸው በሽታ ነጻ የሚያድርግ ታምር አይኖርም። ለማንኛውም እነዚህን ሁሉ አገናዝቦ የህሊና ዳኝነት የመስጠቱን ሐላፊት የምተወው አሁንም ለኢትዮጵያውያን ነው። እኔ ግን የትግራይን ሕዝብ ከወያኔዎች ጋር በአንድ ሙገጫ ውስጥ አስገብቶ አብሮ ፈጭቷል ብለው ከፈረጁኝ ቀደኛ ጠላታቸው ቀርቶ ጌታ በአካል ወርዶ ቢነግራቸው እንኳ እውነትን በእውነትነቱ ላለመቀበል ምለው የተወለዱ ናቸው



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የሚባልላቸው የክህደት ሐዋርያት በመሆናቸው አምነው ይቀበሉታል የሚል ግምት ባይኖረኝም አንባቢዎች ምናልባት በህሊናቸው የሚጉላላ ጥርጣሬ ቢኖር ግልጽ ለማድረግ ስል በምን ዓላማ ላይ ተመስርቸ ስታገል እንደኖርኩ ከዚህ ቀደም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደጋግሜ የገለጽኩትን መለስ ብየ እንድጠቅስ ከደርግ አባልነቴና ከሥልጣን ጥያቄ ጋር አያይዘው ያስመሰሉበት አባባላቸው ገፋፍቶኛል።

በመሠረቱ የምታገልለት ዓላማ **”እናት አገር ኢትዮጵያን ወደጥንታዊ ታሪኳ፣ ስምና ክብረ ወሰነዋ ለመመለስ”** መሆኑን በብዙ አጋጣሚወች ገልጫለሁ። ስለደርግ አባልነቴም ቢሆን **“እኔ በግል ኃላፊነቴ ከገበያ የማይገኘውን የሰው ሕይወት ልነካ ቀርቶ ተሠርቶ የሚገኝ ሐብትና ንብረት ወስደህብኛል ብሎ የሚመሰክር አንድም እውነተኛ የሆነ ኢትዮጵያዊ አይኖርም። ለዚህም እውነተኛ ዳኛ ካለ ሥራየንና ተዘዋውሬ የአገለገልኩበትን ሕዝብ ምስክር አድርጌ እፋረዳለሁ። እንዲያውም ለልጆቼና ለቅርብ ወገኖቸ የማወርሳቸው አንጡራ ሐብትና ቋሚ ቅርስ ብትኖረኝ ይህችው ያልተጎዳደፈች ስሜ ብቻ ናት። በደርግ መንግሥት የጋራ የአመራር ኃላፊነቴ ግን ከእኔ በበለጠ የእናት አገሬና የወገኔ ደመኛ ጠላት የሆኑት ሻቢያና ወያኔዎች ለማጥፊያ የፖለቲካ ጥቅማቸው ሲሉ በሰጡት ትርጉም ሳይሆን በጅምላው የሆይ ሆይታ አሠራር በደረሰው እልቂትና መታመስ አገሬንና ወገኔን አልበደልኩም አልልም። ሌላው ቢቀር ሕዝቡን እኛ የአዋከብነውና የአሳዘንነው አልበቃ ያለ ይመስል የታሪካዊ ጠላቶቹ ቅጥረኛ ሆነው ለዘመቱበት ዳግማዊ ጥቁር ሹምባሾች አሳልፈን መስጠታችን ከዚያ በፊት ከፈጸምነው ወንጀል ሁሉ የከበደ ነው። ብቻ ለዚህ ወንጀል ሕዝባዊ ችሎትም ሆነ የመክሰሻና የመቅጫው አንቀጽ ገና አልተዘጋጀለትም። ይኸም ሆኖ ደርግ የገደለው፣ አስሮ የአሰቃየውና ያሰደደው በዘርና በሃይማኖት ለይቶ ሳይሆን፣ የአገሪቱን አንድነት የሚያራምድበትን ሥርዓትና የያዘውን ሥልጣን ይቀናቀኑኛል የሚላቸውን ሁሉ ነው። በዚህ ወንጀሉም ከሳሽ፣ ምስክርና ፈራጅ ሆኖ የሚጠይቀው የጉዳቱም ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጅ ጠላቶቹ አይሆኑም። ጠላት ዳኛ አይሆንምና። እኔም በጋራ የአመራር ኃላፊነቴ በአደረስኩት በደል በሕይወት ከአለሁ ቁሜ፣ ከሌለሁም ስምና ታሪኬ ቀርቦ ሊፈረድበት ይገባል።...እስካሁን ስታገል የቆየሁትና ወደፊይም የምታገለው በደርግ አባልነቴ ከተሸከምኩት የተጠያቂነት እዳ ለመቀነስና የበደልኳቸውን አገርና ሕዝብ ለመካስ እንጅ የሞተ ደርግን ከመቃበር አውጥቸ ለመመለስ አለመሆኑን ገና ከመነሻው ጀምሮ በግልጽ አሳውቄያለሁ”**Ethiopian Regiter vol.5, no.3, March1998. ገጽ56-57. አንብቦ ማረጋገጥ ይቻላል። የደደቢት መርዝ ቀማሚዎችና የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ማፍረሻ ፈንጅ አጥማጆች የሆኑት አዲስ ምልስ ወያኔዎች ግን በዚህ መልክ እራሳቸውን አዘጋጅተው ወደ ኢትዮጵያን ሕዝብ አልቀረቡም። አቶ ገብረ መድህን አርዓያን ሳይጨምር ማለት ነው። እንዲያውም በተቃራኒው **"የኢትዮጵያ ሕዝብ ምህረት በሚጠየቅበት የእድገት ደረጃ ላይ አይደለም"** ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው እንደሆነ የማይገባው ካለ እነሱን የሚመስል መሆን አለበት።

ሌላው ዶክተሩ በእጅጉ የሚያሳዝን ነው ብለው ለማስመሰል የቀባቡት "የቀድሞው የኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ኃይል አባል የነበሩ ብ/ጄኔራል ኃይሌ መለሰ በፈቃዳቸው የዚህ የከረፉና አገር አፍራሽ የጥላቻ አራማጆች ካምፕን መቀላቀላቸው ነው” (ገጽ3) ብለው ኮንነውኛል። ከዚህ ጋር አዛምጀ ዘረኞች ለበተኑት ችግር ትምህርት ሰጭ የሆነ አንድ ምሳሌያዊ አነጋገር መጥቀስ አፈልጋለሁ። የመንግሥት አዋጆች በየገብያው በሚነገርበት የድሮው ዘመነ “በየወገንህ ተሰባሰብ ተብሎ ቢታወጅ ቁርበት እየተንከባለለ ሄዶ ከብቶች ተራ ተሠለፈ” ይባላል። ለእኔ ይኸ ቀላል መልዕክት ያለው አባባል አይደለም። ታላቁ ፍጡር የሰው ልጅ ቀርቶ በድኑ ቁርበት እንኳ ወገኑን ፈልጎ ሄዶ እንዲሰለፍ የተገደደበት አንድ መሠረታዊ የሆነ ችግር መኖሩን ያመልክታል። በየወገንህ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ሲባል ደግሞ ቁርበቱ የከብቶችን ተራ ፈልጎ ሄዶ እንደተቀላቀለ ሁሉ የሰው ልጅም በሰውነቱ ሰዎች ወደሚኖሩበት አደባባይ ወጥቶ ይቀላቀላል ማለት እንጅ ከሰዎች እየራቀ ሄዶ ጫካ በመግባት የአውሬዎች ባህሪይ ወርሶ ሰዎችን እየበላ ለመጨረስ ይዘምታል ማለት አይደለም። ከዚህ ግንዛቤ አንጻር እነሱ ከብሔራዊ የአንድነት መድረክ በፈቃዳቸው ወርደው ወደመንደራቸው እየዘቀጡ በመሄድ በወረሱት የአውሬነት ባህሪይ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ሲዘምቱ እኔ በሁለመናችን ላይ የዘመቱ የጥፋት ዓላማ አራማጆችን ለመከላከል ከተዘጋጁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቸ ጋር ሄጀ ብቀላቀል ሊያሳዝናቸው ባልተገባም ነበር። ከማዘንም አልፎ የደም እንባ ቢያለቅሱ እንኳ ሳያስፈልግ ፈልገው ያመጡት ችግር ለእነሱ ብቻ ዋጋቸውን ከሚከፍላቸው በስተቀር ይህን ስንለው ከሚያካሄደው ትግል ይገታል የሚል ተስፋ አሳድረው ከሆነ የሰውን ልክ ካለማወቅ የመጣ ከንቱ ቅዠት ነው።

ሌላው ሄዶ ተቀላቀለ የተባልኩበት ካምፕ የከረፋና አገር አፍራሽ የጥላቻ አራማጆች ክምፕ ነው መባሉ ነው። አገር አፍራሽ የጥላቻ አራማጆች ናቸው ስለተባሉት ኢትዮጵያዊያን በራሱ አርዕስት ስለምመለስበት በዚህ ላይ አልገፋበትም። በዚህ አርዕስት ስር የማተኩረው ግን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነታችን የምንሰባሰብበት ካምፕ የከረፋ ስለመባሉ ነው። ወያኔዎችን በብዙ መልኩ እንደገመገምኳቸው በበከላቸው የዘረኝነት በሽታ ምክንያት አምስቱን ህዋሳት ያጡ ወይም በሽታቸው የገደላባቸው ይመስለኛል። እንዲህ ያለው ችግር ባይኖርባቸውማ ኖሮ በአሁኑ ወቅት ከእነሱ የባሰ በዘር በሽታ ተበክሎ የሚከረፋ፣ ግምቶ የተላና የአገሪቱን ጤናማ አየር በክሎ ሕዝቧን ጤና ያሳጣ፣ ፍቅርን በጥላቻ ለውጦ ጠላትነትን የገዛ፣ አገሪቱን እየቸረቸረ መቅኖ ያሳጣና ሉአላዊነቷን ደጋግሞ ያስጠቃ ማንና የት የከፋና የከረፋ አለ? ከእነሱስ የባሰ የራሳቸው የዘረኝነት ግማትና ክርፋት የማይሸታቸው፣ ውድመትና ጥፋታቸው የማይታይቸው፣ ክህደት አምልኮታቸውና ጥፋት ግብራቸው የሆኑ መርገምቶችቶ የትኛው አገርና ዓለም አለ? በመሠረቱ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ማህል ለዘመናት ያልነበረ ዘረኝነትን፣ ጥላቻና ጠላትነትን ዘርተው ያበቀሉ፣ ኮትኩተው ያሳደጉና እየወጋ ሲያቋስልና ሲያዳማ የሚኖር መርዘኛ እሾህ እንዲያፈራ ያደረጉ እነሱ ናቸው። እንዲህ ያለውን መርዘኛ እሾህ በመላ አገሪቱ ዘርተው ያራቡት ደግም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን አምርረው ከመጥላታቸውና አሽቀንጥረው ከመጣላቸው በመጣ ድህነት ነው። እኔንም ሆነ አብረው የፈረጇቸውን ወገኖቸን ግን እንደ እነሱ ክህደት አላጠቃንም፤ የእምነት ድህነትም አልወረሰንም። በዚህ ድህነት ምክንያት የሚመጣ የዘር በሽታም አልለከፈንም። የእኛ ጥፋት በአገርና በሕዝብ ላይ የዘመቱ የጥፋት መልዕክተኞችን አውቀንባችኋል ብለን በግልጽ መናገራችን ነው። ዘረኝነታቸው አርቆ የማሰብና ተገላምጠ የማየት አድማሳቸውን ያጨለመባቸው ዓይነ ሥውሮች በእነሱ ዓይን የሚያዩት ሁሉ ዘረኛ ነው ከተባለ ግን እኛም ብቻ ሳንሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ዘረኛ ነው ማለት ነው።

ስለዚህ ቢማጸኑኝ እንኳ የእነሱን እምነትና ግብር አልወርስም። ምክንያቱም የሁላችንም የሆነችውን እናት አገር እንደ እኔ የሚወዱልኝንና ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ጋር ተዋደው የሚኖሩትን ወገኖቸን ክምንም ተነስቸ የምጠላበትና በጠላትነት የምፈርጅበት የአውሬነት ባህሪይ ፈጽሞ ስለሌለኝ ነው። በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነቴ ላይ ለሚመጡ ጠላቶች ግን ለማንም ቢሆን መቸ ይቅርታ የለኝም። ጆሮ ለራሱ ባዳ ነው እንደሚባለው ከወያኔዎች የሚወጣው የዘረኝነት በሽታ ግማትና ክርፋት በኢትዮጵያዊያን ዘንድ በእጅጉ የተጠላባቸው መሆኑን ያወቁ አልመሰለኝም። ቢያውቁም መጠላት የእነሱ የክብር መግለጫ ስለሆነ ግድ የላቸውም። ከዚህ በተቃራኒው የኢትዮጵያውያን ጽኑ እምነት፣ ጤናማ ፍቅርና መልካም ሥራ ሁሉ ለእነሱ የማይስማማ ጠረን ነው። በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ወያኔወች የአሉበት አካባቢ ሁሉ እንደ ቄራ አካባቢ (የቄራን አካባቢስ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በኬሚካል መከላከል እየተቻለ ነው) በሩቁ የሚገማቸውና የሚከረፋቸው ሆነዋል። እንዲያውም የተባብሩት መንግሥታት እስከ አሁን የነበረው ልምድ ዘረኝነት የሚስፋፋው በበሽታው በተበከሉና አምልኮቱን በሚያመልኩ ሰዎች መካከል የሚፈጠር እንጅ አገርን አብሮ የሚበክልና የሚያጠፋ አልነበረም። ወያኔዎች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የዘሩት የዘረኝነት በሽታና ግማት ግን ከኢትዮጵያም አልፎ ዓለምን የሚበክልና እስክ አሁንም ታይቶ ያልታወቀ አደገኛ ወረርሽኝ መሆኑን አውቆ መከላከያ ክትባት ለማዘጋጀት ቢያስብ ለምርምር ያለአማራጭ የሚወስደው የወያኔዎችን የተበከለ ደም ሳይሆን አይቀርም ብየ ብናገር ስህተት እንዳልሆነ ህሊናቸው ያውቃል። ከዚህ ችግር ጋር አዛምዶ በጸረ ፋሽስትና ቅኝ አገዛዝ ተጋድሎው ታሪክ ደጋግሞ ያረጋገጠለት የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት ለእናት አገሩ፣ለሰንደቅ ዓላማውና ለብሔራዊ ክብሩ አንድ ሆኖ እንዲዘምት ሲያደርጉት የኖሩት እነዚያ የወንድማማችነት ፍቅርና የእርስ በርስ መተሳሰብ ዛሬም መኖራቸውን ለማረጋገጥ ፈልጎ አንድ መጥይቅ አዘጋጅቶ ቢያሠራጭና ከመጥይቆቹ ውስጥ እንደድሮው በመካከላችሁ ፍቅርና መተሳስብ አለን? ከሌለስ በምን ምክንያት?ከሰዎች የምትጠላው ማነን ነው? ከምግብስ?የሚሉ ጥያቄዎች ተካተው ቢቀርቡለት፣ ወያኔዎች በዳበረ ልምዳቸው የምርጫ ካርዱን ገልብጠው ካልወሰዱበት በስተቀር የሕዝቡ መልስ ምን ሊሆን እንደሚችል አንባቢዎች ተመራምረው መልስ እንዲሰጡበት አቅርቤያለሁ። እምነተ-ጽኑዕ፣ ምግባረ ጨዋና ሰው አክባሪ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለበቂ ምክንያት ወገኑን ቀርቶ ጠላቱን እንኳ ቀድሞ የሚጠላ ባህልና ልምድ ፈጽሞ አልነበረውም፤ የለውምም። የትግራይ ሕዝብ በምን እንደሚተረጉመው ባላውቅም ልጆቹ ግን በእሱ ስምና መሳሪያነት ሲያካሂዱ የኖሩት ድርጊት ግን ከመጠላትም አልፎ በለየለት ጠላትነት የሚያሰላልፍ እየሆነ መምጣቱ የሚያጠያይቅ አልሆነም። ምክንያቱም አገር አጥፊ ልጆቹ ባለፉት 20 ዓመታት የሌላውን ኢትዮጵያዊ ልጁንና ቤተሰቡን፣ ጎረቤቱንና ወገኑን ሲገድሉ አይቷቸዋል፤ ነፍስ ያላወቁ ህጻናትን እየገደሉ ጎዳና ላይ ሲጥሉ፣ ልጣቸው ተርሶና መቃብራቸው ተምሶ የጥሪ ቀናቸውን የሚጠብቁ አዛውንቶችን እስር ቤት በማጎር በወጉ የመሸኘት አድል ያሳጧቸው እነሱ መሆናቸውም ያውቃል። አስረው ሲያሰቃዩ፣ እየደበደቡ አካል ሲያጎሉ፣ ፍትህን አዛብተው ሲፈርዱ የሚያያቸውም እነሱ ናቸው። ከጎስቋላ ኑሮው እያፈናቀሉ ንብረቱን ሲዘርፉ፣ ከትዳሩ አፋትተው ሚስቱን ሲውርሱ የሚያያቸውም እነሱኑ ነው። የትግራይ ሪፐብሊክን ግዛት ለማስፋፋትና የሕዝቧን ቁጥር ለማብዛት ሲባል በወረራ የያዙትን ክልልና በግድ ትግሬ መሆን አለብህ ብለው በሚያሰቃዩት ሕዝብ ላይ የሚፈጽሙትን ግፍና በደልም ደህና አድርጎ ያውቃል። ባለሞያ ሠራተኞችን እያፈናቀሉና ነቅለው እያሰደዱ በሁሉም ቦታ ተሰግስገው በመግባት የሚያደርጉትን ሁሉ ጠንቅቆ ያውቃል። የእናታቸውን ጡት ጠብተው ያልጠገቡትንና (በወያኔዎች ጊዜ የሚደርቅ እንጅ የሚያግት ጡት ባይኖርም) ከክንዳቸው ያልወረዱትን ህጻናት ወደ አውሮፓ፣ ወላጆች ከዓይናቸው እንዲርቁ የማይፈልጓቸውን ልጃገረዶች ደግሞ ወደአረብ አገሮች ያለመድህን እየሸጡ መነገጃ በማድረጋቸውና የውቅያኖስ ቀለብ ሆነው እንዲቀሩ በማድረጋቸው የስንቶቹን ወላጆች ማህጸን እንዳሳረሩና ማቅ አስለብሰው እንዳሳዘኑ ደህና አድርጎ ያውቃል። በቀን ሦስት ጊዜ እንመግብሀለን ተብሎ የተደኮሰረለት ሕዝብ የረሀቡ መክሊያ እንኳ አጥቶ ጉርሻ እየገዛ እንዲኖር መገደዱንና እጅግ በከፋ ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ እንዲኖር መገደዱንም የየዕለት ኑሮው እየነገረው ነው። ቤተ ክርስቲያንና መስጊድ፣ ገዳምና ገጠር፣ ገብያና አደባባይ ሳይለይ ሲካሄድ የኖረውንም አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ያውቃል። የእናት አገሩን አንድነትና የባህር በሯን እነማን እንዳናጉትና እንደዘጉት፣ ማህልና ዳር ደንበሯን ሳይለዩ እየሸነሸኑ በመሸጥ ላይ ያሉትም እነማን እንደሆኑ ጠንቅቆ ያውቃል። ሌላው አንገቱን ደፍቶ እያዘነና እየተገዛ በሚኖርባትና ከ14 ሚሊዮን በላኢ የሆነ ሕዝብ የዕለት ደራሽ ምግብ በተጠየቀበት አገር ሳይሠሩ በልጽገውና ሳይሾሙ ነግሠው መሬት ጠበበችን ብለው ዘወትር ሲቦርቁ የሚኖሩት እነማን



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

እንደሆኑም ያውቃል። የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል እንደሚባለው የአገሪቱን ሐብት እየተሻሙ ለመቀራመትና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሚጥጠው ለመክበር ሲሉ (አገር እየሸጡ መክበር ባይገኝም) በሚያሳዩት ይሉኝታ የለሽ ስግብግብነት እንደ አገር ነዋሪ ሰው ሳይሆን እንዲያውም እህል ቀምሰውና ገንዘብ አይተው የማያውቁ ሁሉን ለእኔ ባይ ይሉኝታ ቢስ ስግብግብ ሰዎች ናቸው እንዴ በሚያሰኝ ትዝብት ላይ መውደቃቸውንም ያውቃል። ያውቃል።ሌሎቹ አካባቢዎች እየተራቆቱና እየተሟጠጡ ለትግራይ ሁለንተናዊ ግንባታ ሌት ተቀን የሚጋዘውን ሐብትና ንብረት፣የአገሪቱ ርዕሰ ከተማ የቀን ጨለማ ውጧት በትግራይ ክልል ግን የ24 ሰዓት የመብራት አገልግሎት እንደሚሰጥም ያውቃል። በአጠቃላይም የትግራይ ሕዝብ እነዚህን ሁሉ ችግሮች ጠንቅቆ እንደሚያውቅና ለምን በዝምታ ሲመለከታቸው እንደኖረም ከነምክንያቱ ደህና አድርጎ ያውቃል። ስለዚህ እነዚህ ሁሉ ሲፈጸሙበት የሕግ ምስክር ሆኖ ሲያይና ተሸካሚ ሆኖ ሲያስተናግድ የኖረን የኢትዮጵያ ሕዝብ እሮሮ መግለጼ ዘረኛ አድርጎ ሊያስወነጅለኝ ይገባልን? የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እነዚህ ሁሉ እጅግ ከባድና መራራ ችግሮች እየተፈራረቁበት ኸረ ተው!የእስካሁኑ ይብቃችሁ እያለ ጩሆም ብቻ ሳይሆን እያለቀሰም ጠይቋቸዋል። እነሱ ግን ይኸ ሁሉ የጀግንነታቸው ብልጫ፣ የልዩ ሰውነታቸው መገለጫና ህያው የሆነ ነዋሪነታቸው ማረጋገጫ እንደሆነ አድርገው ስለተረጎሙት ችግር የሚታያቸውና ጩኸቱ የሚሰማቸው አልሆነም። ካሁን በኋል ግን የፈጠሩት ችግር ሁሉ ተመልሶ ከፈጣሪዎቹ ጋር እንዲጣል አድርጎ ከማስተናገድ ውጭ ሌላ አማራጭ መፍትሄ ፈጽሞ የለም።

በተለየም እኔ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን የተለየሁ ባልሆንም በሦስት አቅጣጫ ያደረሳችሁብኝ ቁስል መቸም ይሁን የት እንድረሳችሁ አያደርገኝም። ከአማራነቴ በላይ አልቄ በማየው ኢትዮጵያዊነቴ መጥታችሁብኝ ቀርቶ በአማራነቴ እንኳ እናንተ አማራን ለማጥፋት ስትዘምቱ አማራ መጥፋት የለበትም ብለው በጽናት ከቆሙት ብሔራዊ ታጋዮች ጎራ ብቀላቀል አይድነቃችሁ። ይህን ስል ግን በይፋ አውጇችሁ የተነሳችሁበትን ሕዝብ ለመግለጽ እንጅ በሌሎቹም በኦሮሞው፣ በጉራጌው፣ በአፋሩ በሱማሌው፣ በጋምቤላው፣ ወዘተ ላይ የተፈጸመው ግፍና በደል ሁሉ የሚሰማኝ እኩል ነው። በሞያየ መስክ ደግሞ የአገሪቱን ብሔራዊ የመከላከያ ኃይል በጠላትነት ፈርጃችሁ እንዳፈረሳችሁት ሁሉ እናንተን መልሶ የሚያፈራርስና የበደላችሁ ዋጋ የሚያስከፍል አጋጣሚ እስከሚፈጠር ድረስ የሚቻለኝን ሁሉ ከማድረግ የምገታ አይደለሁም። የእነዚያን ሁሉ ጀግኖች ደምና አጽም ዘንግቸ ተደላድዬ እንድቀመጥ ኅሊናየም ሆነ የሞያ ግዴታየ አይፈቅዱልኝም። ጣምራ ግዴታየም እነዚህን ሁሉ በታሪክና በትውልድ ሲያፈራርዱ የሚኖሩ ግፍና በደሎችን በፈጸሙ ደመኛ ጠላቶች ላይ አዝማች መኮነን ሆኖ ማዝመትና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ አሽቀንጥሮ በመጣል የራሳቸው ክህደት በቆፈረላቸው አንጋዳ እነሱ ብቻ እንዲቀበሩበት ማድረግ ነው። ይህን ደግም እናንተ በመሰላችሁ (አመለጠ፣ ፓርቲና መንግሥትን አልለየም፣ ጽንፋኛ ነው፣ ከዘረኞች ጎራ ተቀላቀል) ወዘተ እያላችሁ ብተረጉሙኝም እኔ ግን ከመነሻው ጀምሮ ጠንቅቄ ስለማውቃችሁ ትላንትም ፊት ለፊት ገጥሜ ተፋልሜያችኋለሁ፤ ወደፊትም የማደርግበት አጋጣሚዎች ሲገጣጠሙ አደርገዋለሁ።

"ጽኑዕ ጠላት እንደ ጽኑዕ ወዳጅ ይቆጠራል" እንደሚባለው ከእነ ዶ/ር አረጋዊ በረሄ የማስመሰያ ተቆርቋሪነት ይልቅ የአቶ ስብሐት ነጋን የለየለት ጠላትነት እመርጣለሁ። ***"አብረን አልኖርንም፤ ወርቅና አፈር አይቀላቀልም፤ እኛ ካልገዛን ኢትዮጵያን እናጠፋታለን፤ በኤርትራ የመጣ ወዮለት፤ ወዘተ"*** አቶ ስብሐት ነጋ አዲስ አበባ ከገቡ በኋል ያመለኩት እምነትና የቀመሯቸው ቃላት አይደሉም።ግንባር ቀደም መስራቾቹና ግብረ አጋሮቻቸው ሁሉ አብረው ሲያቦኩትና ሲያበስሉት የኖሩት እምነት፣ ሲሰልቋቸው የኖሩት ቃላት ናቸው። ልዩነቱ አቶ ስብሐት ነጋ በግልጽ መናገራቸው ብቻ ነው። ዛሬም አዲስ ሰው መስለው ሊያታልሉን የሚፈልጉት ሁሉ በጀርባቸው ይኸን ሁሉ ጉድ አዝለው የሚኖሩ መሆናቸው ሊገባን ይገባል። የችግር ዳፋቸውን ሁሉ ተሸክመን



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ስንኀብጥላቸው ለመኖር ትዕግስቱም ሆነ ጊዜው የለንም የምለውም በዚህ ምክንያት ነው። የእነሱ የማስመሰያ ኢትዮጵያዊ ተቆርቋሪነት ለዕለት ደስታ ብላ ባልባሌ ቦታ ስትንገላወድ ክብረ-ንጽህናዋን ያስደፈረች ልጃገረድ ይመለስልኛል ብላ እንደመመኘት የሚቆጠር ነው። በመሠረቱ ሰውን ያለአግባብ መጥላትና በጠላትነት መፈረጅ በራስ ላይ ብዙ መዘዝ መጋበዝ ነው። ሌሎቹን ሁሉ አጥፍተው እነሱን ብቻ አደላድለው ለማኖር ሲሉ በፈጠሩት ጠላትነት እንደ ኢትዮጵያ መንግሥት ተቆጥረው ተሸክሚቸው ለመኖር ቀርቶ በሎሌነት ተቀጥረው እየሠሩ ለመኖር እንኳ እድል የሚሰጣቸው አይመስለኝም። በህይወት ያለው ቀርቶ በየአካባቢው የከሰከሱት አጽምና ያጎረፉት የንጹሀን ደም እየወጋ የሚያቆስላቸውና እያንዣለጠ የሚጥላቸው መሆኑ አያጠያይቅም። ባጭሩ በነጻ መንቀሳቀስ የሚችሉበት አካባቢና በፍቅር የሚያያቸው ሕዝብ ፈጽሞ የለም። በክህደት የተጀመረው እቅድና በዳንኪራ የታጀበው ዘመቻ መደምደሚያው ከዚህ ውጭ እንደማይሆን ግልጽ ይመስለኛል። በመጨረሻ የምለው ቢኖር ዶ/ር አረጋዊ በተለመደ አስመሳይነታቸው **“ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ! ውድቀት ለዘረኞችና በታኞች”** በሚል መፈክር ጽሁፋቸውን አጠቃለዋል። የእኛም ጽኑዕ እምነት መግለጫና የማዕዘን ድንጋይ የሆነው መፈክራችን ይኸው ስለሆነ ከልብ እንቀበለወታለን። ለሁላችንም እንደሥራችን የሚከፍለውን አምላክ የምንጠይቀው ቢኖር ለኢትዮጵያ እንደልብወ ክህደት ሳይሆን እንደቃለው፣ እንዲያደርግላት፣ ለእርሰዎ ደግሞ የራስዎ እርግማን በእናንተው ላይ ተመልሶ እንዲውል ቅዱስ ፈቃዱ እንዲሆን ነው። አሜን!!!

(ክፍል ሦስት ይቀጥላል)



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com